# ጥላ TILA

ጥላ የካቲት 2004 ዓ.ም አንደኛ ዓመት ቁ 1 TILA February 2012 First Year 1st Edition

# ወያኔን ያናጋው የኦነግ ውሳኔ!!

ኦብነግስ ምን አስቧል?



ልዩ ቃለ-ምልልስ ከኦነግ ዋና ፀሃፊ አቶ አሚን ጁንዲ ጋር

## Harassment tool – Ethiopian anti Terrorism Law

## ዛምቢያ—የአፍሪካ ዋንጫ ንጉስ









# ማስታወቂያ

በጀርመን አገር በሚታተሙት መፅሄቶች የህትመት ጊዜ ርዝመት ምክንያት ሃሳቦትን/ፅሁፎትን በአፋጣኝ ለንባብ ለማብቃት ተቸግረዋል?የስብሰባና የሰላማዊ ሰልፍ ፎቶዎቾስ በኢንተርኔት እንዲለቀቅሎት ይፈልጋሉ? እንግዲያውስ በአገሪቱ ጠበቆች አድናቆትና እውቅና የተቸረው ጥላ መፅሄት ፈጣንና ፍላጎቶን አርኪ አገልግሎት ለመስጠት ተዘጋጅቷል።

እኛን ለማግኘት ሶስተኛ ወገን አያስፈልጎትም!በቀጥታ ይደውሉልን መረጃዎትን ተቀብለን ፍላጎቶን እናሟላለን።

በአሜሪካና በአውሮፓ ከሚገኙ አገር በቀል መገናኛ ብዙሃን ጋር ባለን ግንኙነት መሰረት በጥላ መፅሄትና ዌብ ሳይት መረጃዎትን አስተላለፉ ማለት ምን አለፉዎት አላማዎት ተሳካ ማለት ነው።
እንግዲያውስ በፈለጉት ቀንና ሰዓት በተለመዱት አድራሻዎቻችን ያገኙናል፡፡

Mesfin Abraha
Wehneberger Straße 63
36251 Bad Hesfeld
Tel. 0152 2219 5567
0176 5938 4456
E-Mail. tilamagazine@yahoo.de
Web-Site. tilamagazine.yolasite.com

ጥላ መፅሄት የእናንተው መጽሄት ናት!

# ጥላ


ዋና ስራ አስኪያጅ — General Manager
መስፍን አብርሃ — Mesfin Abraha

ዋና አዘጋጆች — Editor In Chiefs
እየሩሳሌም ሱሞሮ — Eyerusalem Sumoro
ብሩክ ገ/መስቀል — Biruk G/Meskel
ዳዊት ፋንታ — Dawit Fanta

ፅሁፍ አስተባባሪዎች — Coordinators
ብሩክ ሃይሉ — Biruk Hailu
ዮሴፍ ክፍሌ — Yosef Kifle
ኤደን ዳዊት — Eden Dawit

የኮምፒዩተር ፅሁፍ ቅንብር — Computer Graphics
ቴዎድሮስ ከበደ — Tewodros Kebede
ዮሃንስ ሳምሶን — Yohannes Samson

ሌይአውትና ዲዛይን — Layout & design
እየሩሳሌም ሱሞሮ — Eyerusalem Sumoro

የካርቱን ስዕል — Cartoonist
ብሩክ ገ/መስቀል — Biruk G/Meskel



የጥላ መፅሄት አድራሻ /Tila Magazine Address
Mesfin Abraha
Wehneberger Str.63
36251 Bad Hersfeld
E-Mail:- tilamagazine@yahoo.de
Web- Site:- tilamagazine.yolasite.com
http://www.facebook.com/pages/Tila-Magazine/331232533579176
Tel.No.:- 0152 22195567
0176 59384456
0176 68830082

# ማውጫ


| | ገጽ |
|---|---|
| ውሳኔያችን ወያኔን ከመቼውም ጊዜ በላይ ስጋት ውስጥ ጥሎታል! | 7 |
| ደም መፋሰሱ ይብቃ! | 11 |
| አንድ ኢትዮጵያን እንታደጋት | 11 |
| ትግላችን ከልብ ይሁን | 11 |
| ከዘላለም ባርነት የአንድ ቀን ነጻነት | 11 |
| የኢትዮጵያ መከላከያ ሲፈተሽ | 11 |
| ሆ ብለን እንነሳ | 12 |
| የታሪክ አሻራ ሲጠፋ በዘረኞች | 12 |
| ወያኔዎች የተንኮል ጉድጓድ አትቆፍሩ የሚገባበት አይታወቅምና | 13 |
| አምባገነኑ የወያኔ መንግስት | 13 |
| ኢህአዴግ እና አደገኛ ስትራቴጂው | 13 |
| ሁሉም ይንቃ | 14 |
| የማሕበራዊ ድሕረ ገጾች ፖለቲካዊ ፋይዳ | 14 |
| መታገል አለብን | 14 |
| ግዜው ቅርብ ነው | 15 |
| ህዝባችንን ልንደርስለት ይገባል | 15 |
| ወያኔ እጁን ከሃይማኖት ተቋማት ላይ ያንሳ! | 15 |
| ትግሉን እንቀጥል | 15 |
| ሃሳብን የመግለጽ መብት በፎቶ | 16 |
| የገና ስጦታ | 17 |
| ወያኔ ያተረፈልን | 17 |
| ዴሞክራሲን የማያቅ መንግስት በሃይል ይወድቃል! | 17 |
| ማሞ ሌላ ፎቶው ሌላ | 18 |
| ምን ማድረግ ይገባናል? | 18 |
| ኢትዮጵያ መጨረሻዋ ምን ይሆን? | 18 |
| ውድቀት ለወያኔ | 18 |
| ፍርሃትን ማሸነፍ፤ ወያኔን ማስወገድ | 18 |
| የፖለቲካ ምህዳር በኢትዮጵያ | 19 |
| የሕዝባችን እጣ ፋንታ | 19 |
| ፍትህ ያጣ ሕዝብ | 19 |
| ወያኔ በሴቶች ላይ የሚያደርሰው በደል ይበቃል | 20 |
| በህብረት እንነሳ | 20 |
| ነጻነትና ነጻ መውጣት ለኦሮሞ ሕዝብ | 20 |
| ባገሩ የሌለ የትም የለም | 20 |
| የወያኔ የግፍ አገዛዝ ይብቃ | 21 |
| በአንፃራዊነት | 21 |
| ለስደት የዳረገን የወያኔን መንግስት በአንድነት እናስወግደው | 21 |
| ነጻ ምርጫ ናፈቀኝ | 21 |

# ማውጫ


| | ገጽ |
|---|---|
| የወያኔ አገዛዝ ይብቃን | 22 |
| በኦሮሞ ሕዝብ ላይ በደል የሚያደርሰው የመለስ አገዛዝ ይብቃን! | 22 |
| ዘረኝነትን ማዕከል ያደረገው የወያኔ አገዛዝ | 22 |
| በፍጥነት መወገድ ያለበት የወያኔ አገዛዝ | 23 |
| አሁንስ ይበቃል | 23 |
| በጋራ ከሠራን በወያኔ ላይ ተጽእኖ ማምጣት እንችላለን | 23 |
| አሳፋሪው የወያኔ ድርጊት | 23 |
| ጉዞአቸው ወዴት ይሆን? | 24 |
| ይህ ነው ዴሞክራሲ? | 24 |
| ዴሞክራሲያውያን ነን ይላሉ ናቸውን? | 24 |
| ግፍና ጭቆና ይብቃ | 24 |
| የወያኔ እውነተኛ ባሕሪ ሲገለጽ | 25 |
| አንድነታችን... | 25 |
| የካርቶን ስእል | 26 |
| CATCH-22 | 27 |
| Oromiya is calling! | 28 |
| A war Lover Regime! | 28 |
| Harassment tool-`` Ethiopian Anti-terrorism law`` | 29 |
| Stop killing of the Oromo people! | 29 |
| Nothing Pass People´s voice | 30 |
| The Answer is clear | 30 |
| The reason we need to do is as follows | 31 |
| What Will Be the Evidence of Democracy for people of Ethiopia? | 32 |
| Dictator means EPRDF! | 32 |
| Humanity Crisis | 32 |
| We need freedom! | 33 |
| Undercover torturing of people | 34 |
| All round Harassment | 34 |
| So eine Regierung | 35 |
| The End is approaching | 35 |
| The 2011 Rankings (Ethiopia 108th out of 110 countries) | 36 |
| ጠላፊው" ሀሳብ ወለድ ጨዋታ አቤ ቶኪቻው | 37 |
| ወያኔን ለመጣል | 39 |
| ወይ አገሬ | 39 |
| በቃን | 39 |
| አይለይም ወይ ዛሬስ? | 39 |
| የቀበረሽ በላ | 39 |
| የመዳብ ጥይቶቹ ንግስናውን ከፈርኦኖቹ ተረከቡ! | 40 |



# Editorial

## Now or Never!

In this time are we loving
or do we sit here wondering
Why this world isn't turning round
It's now or never
……………………………
In this way are we learning
or do we sit here yearning
…………
Where's the truth for us to use
'Cause all we seem to do is lose
who we are and how we've tried
are we all the same inside
it's now or never to decide…..(**Singer Justin Bieber-Album-My world)**

On bases of the emerging OLF New Year`s decision**. We** are deciding to use as an introduction some but very important part of Bieber`s song lyrics for our this month`s editorial.

In its historic meeting held in Minneapolis, Minnesota [on Dec 30 and 31], the Oromo Liberation Front (OLF) National Council, led by General Kemal Gelchu, made a significant decision that adds the much needed energy to the struggle of the Ethiopian people against Meles Zenawi's regime. In its two day meeting, the OLF National Council examined and amended the long standing political program of the OLF and made a call to all forces of Ethiopia to work together and realize the common goals of the Ethiopian people.

**Tila magazine** strongly believes that sharing a common vision and working together towards a common goal is not just an option but the only option to correct past mistakes and create a country where peace and justice prevails. The historic& heroic decision of the OLF and its willingness to join other democratic forces of Ethiopia is a significant progress in Ethiopian struggle. However, as important as the recent assessment and resolution of the OLF is; it's just the start of a much longer journey that must expand to include many other political forces of Ethiopia too. Unity is now between a tipping point and a point of no return.

Based on this remarkable moment, we would like to urge the Ogaden National Liberation Front (ONLF) to take the same action to end the call of secession from our motherland because of the mal-administration of our past dictatorial regimes.

Now or Never: Saving Ethiopia from political Collapse. Our basic argument is that the country is saddled by crippling government anti-democratic ruling and we don't have much time to fix our extreme political differences. As ex-American President Ronald Reagan memorably asked, "If not now, when?" So, we expect from ONLF surprising news in the near future to fulfill the loophole of Ethiopian politics. **Tila magazine** brings you as usual new faces & ideas, opportunities and a special guest of honor. Have a nice reading!!!

**``Tila Magazine is yours Magazine!!!Tila is a magazine not only you read it, but also you will write on it!``**



# ርዕሰ አንቀጽ

## ዛሬ ወይም መቼም!

በዚህ ጊዜ እያፈቀርን ነው
ወይስ ቁጭ ብለን እያደነቅን ነው
ይህ ዓለም ዞር ብሎ የማያየው ለምነው?
አሁን ወይም መቼም ነው።
...................
በዚህ መንገድ እየተማርን ነው
ወይስ ቁጭ ብለን እየቆዘምን ነው
............
እውነቱ ወዴት ነው ምንጠቀምበት
የእስካሁኑ ሁኔታችን አስመስሎብናል ውድቀት
ግን ሁላችንም ነን በአንድ ቤት?
አሁን ወይም መቼም ነው አንድነት። መሳይ ትርጉም ነው ያለው የጀስቲን ቢበር ዘፈን።

በተራማጁ የኦነግ ክንፍ የፈረንጆቹ አዲስ ዓመት ውሳኔ መሰረት የዚህን ወር የመፅሄታችንን ርዕሰ-አንቀፅ ጀስቲን ቢበር "ዛሬ ወይም መቼም" ብሎ ካቀነቀነው ዜማው ያገኘነውን ጥቂት ግን በጣም ጠቃሚ መልዕክት በመነሻነት ልንጠቀምበት ወሰንን።

በጀነራል ከማል ገልቹ የሚመራው የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ሚኔሶታ አሜሪካ ዲሴምበር 30 እና 31 2011 ባካሄደው ታሪካዊ ብሄራዊ ኮንግረስ የደረሰበት ውሳኔ በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ በተቃውሞ የሚካሄደውን ህዝባዊ ትግል ለማቀጣጠልና ሃይል እንዲያገኝ ለማገዝ ጠቃሚ ሚናን ይጫወታል።ኦነግ ለሁለት ቀናት ባካሄደው ህዝባዊ ስብሰባ ለረጅም ጊዜያት ይዞት የነበረውን የፓርቲውን ፖለቲካዊ ፕሮግራም በማሻሻል በተለያየ ጎራ የተሰለፉት ኢትዮጵያውያን ሃይሎች በጋራ ተሰባስበው ለኢትዮጵያ ህዝቦች የጋራ ፍላጎት በአንድነት እንዲሰለፉም ጥሪውን አቅርቧል።

እንደ ጥላ መፅሄት እምነት በተበታተነ ሁኔታ የሚንቀሳቀሱት ሃይሎች ለአንድ ዓላማ በጋራ ተሰባስበው መዝመታቸው የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ብቸኛው አማራጭ ነው።ስለሆነም ካለፉት ገዢዎች ስህተት በመማር ሰላማዊትና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት ዴሞክራሲያዊ አንድነት ወሳኝ ነው።ታሪካዊውና በጀግንነት የተደረሰበት የኦነግ ውሳኔ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ለመገንባት ከፍተኛ እመርታን ያመጣል።የአሁኑ የኦነግ እንቅስቃሴ ወሳኙን ጉዞ ለመጀመር ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ከመሆኑም ባሻገር ሌሎች ሃይሎችም በኢትዮጵያ ማዕቀፍ ውስጥ እንዲሰባሰቡ በር ይከፍታል። ዴሞክራሲያዊ አንድነት የህይወት ክር መሆን ደረጃ ላይ በመድረሱ ወደማይቀለበስበት ሁኔታ መሻገር አለበት።

በዚህ ታሪካዊ አጋጣሚ መነሻነት የኦጋዴን ብሄራዊ ነፃ አውጪ ግንባር*ኦብነግ*ም እንደ ኦነግ ተመሳሳይ አቋም በመውሰድ የሶማሌ ክልልን ከኢትዮጵያ የመገንጠል ፕሮግራሙን በማስተካከል ብሎም ካለፉት ገዢዎቻችን ስህተት በመማር ወደ አዲሲቷ ኢትዮጵያ ግንባታ እንዲሰባሰብ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

አሁን መይም መቼም!ነው ኢትዮጵያ ከገባችበት ፖለቲካዊ ቀውስ የማዳኛው ጊዜ። የእኛ መሰረታዊ መከራከሪያ ኢትዮጵያ እየተነዳች ያለችው ፀረ-ዴሞክራሲያዊ በሆነ ፈረስ *መንግስት* በመሆኑ በተለይ በተቃዋሚው ጎራ ያለው ሓይል ፅንፈኛ የሆነውን የፖለቲካ ልዩነት ለመጠጋገን እንኳን በቂ ጊዜ ስለሌለው ረጋ ብሎና ግራ ቀኙን አይቶ በፍጥነት ወደ አንድነቱ ባቡር ሊሳፈር ይገባዋል እንላለን።

ያለንበት ወቅት የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሮናልድ ሬገን በአንድ ወቅት የጠየቁትን ጥያቄ እንድንጠይቅ ያስገድደናል።ሰውየው "አሁን ካልሆነ ታዲያ መቼ ነው?" ነበር ያሉት።ስለዚህ በቅርቡ ከኦብነግ በአገሪቱ ፖለቲካ ያለውን ክፍተት እንደሚሞላ የሚገመተውን አስደናቂ(ሰበር) ዜና እንደምንሰማ እናምናለን።ጥላ መፅሄት እንደተለመደው አዳዲስ ፊቶችንና ሃሳቦችን፤ዕድሎችንና ልዩ የክብር እንግዶችን ይዛ ባላችሁበት ደርሳለች።ቤት ለእምቦሳ በሏት።መልካም ንባብ!!!

**"ጥላ መጽሄት የእናንተው መፅሄት ናት!!! ጥላ የሚያነቧት ብቻ ሳትሆን የሚፅፉባትም መጽሄት ናት!"**

# About Tila
# Dear Readers

Realizing the fact that the digital age has empowered and made ordinary people across the world irrepressible beyond their imagination, **WE** aims to serve as a credible platform that will spread uncensored interviews, news, commentaries and analyses that are unlikely to see daylight in Ethiopia.

Fortunately, here is where you find **TILA**, the un-disputably best source of information serving the Ethiopian Diaspora community in Europe & America with a proven record of excellence in journalism.

**TILA** is a political magazine, published and distributed by patriotic Ethiopians around Hessen region in Germany, which appears in Amharic, English and Germany Languages every 3 months. It is a magazine of quality, responsibility and standard. Entertainment and sport are among our coverage issues next to Ethiopian politics.

As a reader, you are to get useful political and current news in **TILA** than any other publication can offer you. More comprehensive analysis and interpretations than any other media can present to you. In fact, these are some of the qualities of **TILA** that has made it the largest circulating magazine in its category. TILA magazine has also partnered with ethiomedia.com, ethiogermany.de and afroaddis.wordpress.com among others, to deliver reliable and high quality content to our visitors.

Don't take the chance of missing this spectacular political magazine. Subscribe to it today!

We promise, you won't regret your decision. Reach us on tilamagazine@yahoo.de & tilamagazine.yolasite.com

**Tila Magazine is yours Magazine!**

# ከአዘጋጆች
# ውድ አንባብያን

ጥላ መፅሄት በየሶስት ወሩ የሚታተም የፖለቲካ መፅሄት ነው።መፅሄቱ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መሰረት አድርጎ በጀርመን አገር የሚታተም ቢሆንም መረጃ መረቦችን በመጠቀም መላውን ዓለም የማዳረስ ዓላማን አንግቦ እየተንቀሳቀሰ ነው።

የአገራችንን ወቅታዊ ሁኔታና ጠቃሚ መረጃዎችን በማካተት ዝናን ያተረፈው የጥምረት መፅሄት አዘጋጆች ያቋቋሙት ጥላ መፅሄት የስሙ ስያሜ እንደሚያመለክተው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች በተበታተነ ሁኔታ የሚያካሂዱትን የትግል ሂደት በማስቀረት በአንድ **ጥላ** ስር እንዲሰባሰቡ ለማሳሰብና አቅጣጫ ለመጠቆም ነው።

የፖለቲካ ሃይሎች በተበታተነ ትግላቸው ጋት እንኳን መራመድ እንደማይችሉ በመገንዘብ የጋራ ትግል እንዲያካሂዱ ለማበረታታትም ጭምር ነው እ.ኤ.አ ከጥር 2012 ጀምሮ በዚህ ስም መፅሄቱ እንዲጠራ የወሰንነው።በመፅሄቱ አዝናኝና አስተማሪ ዝግጅቶች የሚካተቱበት ሲሆን ስፖርትም ትኩረት ያገኛል።

ጥላ መፅሄት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሃሳቡን ያለምንም ገደብ በነፃነት የሚያቀርብበት ክፍት መድረክ በመሆኑ በመፅሄቱ የሚወጡት ፅሁፎች በሙሉ የፀሃፊዎቹን እንጂ የጥላ መፅሄት ዝግጅት ክፍልን የማይመለከቱ መሆናቸውንም መግለፅ እንወዳለን።

**ጥላ መፅሄት የእናንተው መፅሄት ነው!**

# ውሳኔያችን ወያኔን ከመቼውም ጊዜ በላይ ስጋት ውስጥ ጥሎታል!

### አቶ አሚን ጁንዲ የኦነግ ዋና ፀሃፊ



አቶ አሚን ጁንዲ በትግል ስማቸው *በሪ ቦሩ*የኦነግ ከፍተኛ አመራርና ዋና ፀሃፊም ናቸው።ኦነግ ባለንበት የፈረንጆቹ አዲስ ዓመት ለደረሰበት ውሳኔ ከፍተኛ ሚና እንደነበራቸው ከሚነገርላቸው ከእኚሁ ሰው ጋር ከሚኖሩበት ከካናዳ በስልክ ቃለምልልስ አድርገናል። ቃለምልልሱን ባልደረባችን ጋዜጠኛ መስፍን አብርሃ እንደሚከተለው አሰናድቶታል። መልካም ንባብ።

**ጥላ፡-** ኦነግ በቅርቡ በአሜሪካ ሜኒሶታ ላይ ባካሄደው ህዝባዊ ስብሰባ ኦሮሚያን ከኢትዮጵያ የመገንጠል ጥያቄውን እንዳነሳ አውጇል።እዚህ ውሳኔ ላይ ለመድረስ እንዴት ቻላችሁ?አሁን ምን አዲስ ነገር ተገኘ?

**አቶ አሚን፡-** ድርጅታችን እዚህ ታሪካዊ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የቻለው የኢትዮጵያን የኦሮሞ ህዝብን ተጋድሎና የዓለም ፖለቲካን በመገምገም እንዲሁም በአገር ቤት ያለው የኢ-ዴሞክራሲያዊ ስርኣት ዕድሜ ማራዘሚያዎችን ለማሳጠር ያለውን ሁኔታ በማጤን ነው።ምንም እንኳን በወያኔ በኩል አዲስ ነገር ባይኖርም ኦነግ አዲስ አቋም መያዝ መቻሉ ነው አዲሱ ነገር።

**ጥላ፡-** ኦነግ ከ40 ዓመት በላይ በፕሮግራሙ ውስጥ መገንጠልን እንደ ዋነኛ አጀንዳ ይዞ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል።አሁን የደረሳችሁበት ውሳኔ አልዘገየም ይላሉ?

**አቶ አሚን፡-** ውሳኔው አልዘገየም ምንም የዘገየበት ሁኔታ የለም።ሁሉም ክስተቶች የየራሳቸው ዕድሜና ያስመዘገቧቸው ድሎች አሉ።ስለዚህ ይህ ውሳኔ የመወሰኛው ጊዜ ደግሞ አሁን ነው።ወቅቱ አሁን በመሆኑም ዘግይቷል ማለት አልችልም።የኦሮሞ ህዝብ የደረሰበትን ጭቆናና የትግል ሂደት መለስ ብለን ስናይ ዘግይቷል ማለት አንችልም።እስካሁን ይዘነው የቆየነው አቋም የሚያዋጣንና ስኬታማ የሚያደርገን እንዳልሆነ በመረዳት ነው አዲሱ ውሳኔያችን ላይ የደረስነው።

**ጥላ፡-** አሁን የደረሳችሁበት ውሳኔ ቀደም ብሎ የተወሰደ የአቋም ለውጥ ቢሆን ኖሮ ምን ውጤት ይኖረው ነበር?

**አቶ አሚን፡-** ህዝቦች ጥቅምና ጉዳቱን በግልፅ ሳይመለከቱት፤የህዝባችን የፖለቲካና የኢኮኖሚ እድገት ሳይረጋገጥ ወይም ግንዛቤው ሳያድግ ውሳኔው ተወስኖ ቢሆን ኖሮ ከሩዋንዳም የበለጠ ችግር ያጋጥመን ነበር።አሁን ግን የህዝቡ ፖለቲካዊ ግንዛቤ በከፍተኛ ደረጃ በማደጉ የመገንጠል ሁኔታን ይፈራል።ተግባራዊም ያደርገዋል ብዬ አልገምትም።

**ጥላ፡-** የኦሮሞ ህዝብ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሆኖ ኢህአዴግን መታገል ለምን አስፈለገው?ኦነግ በራሱ ብቻውን ቢታገል ምን ይቀርበታል?

**አቶ አሚን፡-** ኦነግ የሚታገለው በዛች አገር ያለውን ግፍ ለማስወገድ ነው።እንዲሁም የኦሮሞ ህዝብ የራሱን ዕድል በራሱ እንዲወስን ነው።በዚህም ያስመዘገባቸው አንፀባራቂ ድሎች አሉ።የኦሮሞ ህዝብ ከብዛቱ ካቀማመጡ ከሁሉም ህዝቦች ጋር የተዋሃደ የተጎራበተ መሆኑን ከተገነዘብን በሁዋላ ነው ነገ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ጋር የእኛ ችግር የእነሱ ችግር የኛ መፍትሄ

## በኢትዮጵያ ህዝባዊ ትግል ታላቅ እርምጃ!

ለረጅም ዓመታት የዘለቀው የኦነግን የመገንጠል መርሕ በመጣል፤ ጥያቄውን በኢትዮጵያ ማእቀፍ ውስጥ ለማስተናገድ ብቅ ያለው የኦነግ ክፍለ-ሃይል ከተጻራሪው ወገን ጋር በአስቸጋሪ ውስጠ-ትግል ላይ እንደነበረ ማገናዘቡ አይከብድም።
ውስጠ-ትግሉ የጫረው የአቋዋም ልዩነትና አንደምታው በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ላይ ትልቅ ቦታ የተሰጠው አነጋጋሪ ጉዳይ ሆኗል። የጋራ ችግሮቻችን በጋራ ተሳትፎ ለማስወገድና ተባብረን በጋራ ለማደግ ሲል ተራማጁ የኦነግ ክፍለ-ሃይል የተራመደው እርምጃ ትልቅ ነው። ለኢትዮጵያ ህዝቦች እኩልነታዊ አንድነትና ለሃገራዊ ሉዓላዊነት የቆመ ዜጋ ሁሉ ይህንን አዲስ እድገት በጸጋ ተቀብሎ ማስተናገድና እንዳይቀለበስም በሳል አስተዋፅኦ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ዶክተር አረጋዊ በርሄ**
**የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር ሊቀመንበርና**
**የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት አመራር አባል**

የእነሱም መፍትሄ ነው በሚል ወያኔ ሁላችንንም እኩል በጋራ ስላሳደደን የጋራ ትግል አስፈልጎን ነው እንጂ ወያኔን ኦነግ ብቻውን ታግሎ አያሸንፈውም ከሚል አይደለም።

**ጥላ፡-** የኦሮሞ ህዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ጋር መታገሉ እንደሚጠቅመው በመግለፅ ብዙ የለፉ ምሁራን ነበሩ።እነዚህን ምሁራን ምን ይሏቸዋል?

**አቶ አሚን፡-** ከማመስገን ሌላ የምንለው ምን አለ ብለህ ነው?ይህ አመለካከት እንደ ዱብ እዳ የመጣ ሳይሆን ለረጅም ጊዜ የተወያየንበትና ያበሰልነው ጉዳይ ነው።አዲሱ አመለካከት የማይወድቅ መሆኑን የሚያመላክተው ለረጅም ጊዜ ተወስዶ ውይይት የተደረገበትና አዋጭነቱ የተረጋገጠ መሆኑም ነው።

**ጥላ፡-** በአዲሱ አቋማችሁ ላይ እስካሁን ያለው የህዝብና የምሁሩ ግብረ-መልስ / feed back/ምን ይመስላል?

**አቶ አሚን፡-** ምሁሩ እንደሚታወቀው የኢትዮጵያን ሁኔታ ከስሜታዊነት ውጭ ረጋ ብሎ የሚያይ በመሆኑና የመለስ ስርዓት ህዝቦችን ከፋፍሎ ብሄሮችን ከብሄሮች በማጋጨት እድሜውን ለማራዘም እንደሚፈልግ ስለሚያጤነው ይህ ውሳኔ የእሱ ከፍተኛ ድል አድርጎ እንደሚወስደው ተረጋግጧል።ህዝቡም ከምሁሩ ባልተናነሰ ሁኔታ ከፍተኛ ድጋፉን እያሳየ ነው።

**ጥላ፡-** በቅርቡ በእንግሊዘኛ ባወጣችሁት መግለጫ መሰረት ``in forming the new federal democratic republic of Ethiopia, the OLF will respect and honor all decisions the Ethiopian people’s will make using their right of self-determination.``ይላል። ይህን ሃሳብ በማየት አሁንም ኦነግ የመገንጠል አላማውን አልተወም ለሚሉ ወገኖች ምን ምላሽ አላችሁ?

**አቶ አሚን፡-** በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ የመገንጠል ጥያቄና የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው።በዴሞክራሲያዊ ስርዓት የምናምን ከሆነ ይህንን ጥያቄ ከህገ መንግስታችን ውስጥ ማውጣት ህገ መንግስትን ማጥፋት መሆኑን ለመግለፅ እንጂ አልሸሹም ዞር አሉ የሚለውን መንገድ ለመከተል አይደለም።ሁሉንም ሂደት አጢነን ከፊታችን



የተጋረጠብንን ሁኔታ አጥንተን እንዲሁም ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት ያለንን ራዕይ በማገናዘብ ነው ይህን አይነኬ መብት በመግለጫችን ያካተትነው።ለዚህም ስጋት ሊኖር አይገባም።

**ጥላ፡-** ይህንኑ አዲስ አቋማችሁን ተንተርሰው አንዳንዶች የኦነግ የፕሮግራም ለውጥ የታክቲክ እንጂ የስትራትጂ ባለመሆኑ በአሁኑ አቋሙ ከወያኔ ኢህአዴግ ጋር ሆኖ ለምን ዓላማውን አያሳካም የሚሉ ወገኖችም አሉ።ምላሾ ምንድን ነው?

**አቶ አሚን፡-** አንደኛ በየዋህነት የተነሳ ጥያቄ ከሆነ ግልፅ አደርጋለሁ።አሁን የተራመድነውን እርምጃ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ መገመት ያልቻሉ ሰዎች ጥያቄውን እንዳነሱት መገመት ይቻላል።ዛሬ እኛ በጀግንነት ትክክለኛው አመለካከት ይሄ ነው ብለን ስንራመድ ተቃዋሚ መሆን ያለበት ወያኔ እንጂ ከእኛው ጎራ መነሳቱ አግራሞትን ይጭራል።

ወያኔ ህዝባችንን በዴሞክራሲና በፌዴራል መንግስት ስም እየገዛ ያለ መንግስት ነው።ወያኔ የሚከተለው ፌዴራሊዝም ትክክለኛ አይደለም።ህዝቦችን ከፋፍሎ ለመግዛትና ፍትሃዊ ያልሆነ የኢኮኖሚ ክፍፍል ለማድረግ የሚጠቀምበት መሳሪያ ነው። ለዚህ ነው ወያኔን የምንቃወመው። የፌዴራሊዝምን ስም በመጥራታችን ከወያኔ ጋር ያገናኝናል ብለን አናምንም።

**ጥላ፡-** በአቶ ዳውድ ኢብሳ የሚመራው ኦነግ የኦሮሞ ህዝብ በአቢሲኒያ ቅኝ ግዛት ስር ነው የሚል አቋም እንደያዘ መቀጠሉ ምንን ያመለክታል ይላሉ?

**አቶ አሚን፡-** ይህን በተመለከተ እራሳቸው ቢጠየቁ ጥሩ ነው።እነሱ የያዙት መንገድ ድል አያመጣም ብለን ትተነው ለቀነዋል።ይሄ የእኛ አመለካከት

## ወቅታዊና ትክክለኛ ውሳኔ!

ኦነግ በቅርቡ የደረሰበት የፕሮግራም ማስተካከያ ውሳኔ የኢትዮጵያ ህዝቦች በሰላም በመተሳሰብ በእኩልነትና በዴሞክራሲያዊ ማዕቀፍ ተባብረው በጋራ ለመኖር ያላቸው ምኞት አስተማማኝ መሰረት እንዲኖረው የበኩሉን ሚና ይጫወታል።

የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች በብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ጥላ ስር መሰባሰባቸው የአምባገነኑን የመለስ ዜናዊ ስርዓት ዕድሜ ለማሳጠር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ስለሚኖረው በጀነራል ከማል ገልቹ የሚመራው ኦነግ ለደረሰበት ውሳኔ ያለንን አድናቆት እንገልፃለን።

ኦነግ የወሰደው አቋም ራሳቸውን ላላስተካከሉ ሃይሎችም አቅጣጫ ጠቋሚ በመሆኑ ከልባችን የምንደግፈው መሆኑን እናስታውቃለን።የኤርትራ መንግስት የኢትዮጵያውያንን አንድነት በመርህ ደረጃ የማይቀበል ስርዓት በመሆኑ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ከኤርትራ ጠቅልሎ በመውጣት በአገር ውስጥ ማድረግ የጀመረውን ትግል ለማጠናከር ኦነግም ሆነ ሌሎች ሃይሎች ትግላቸውን ባገር ውስጥ እንዲያደርጉት ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።ኢትዮጵያውያን ለራሳቸው ችግር መፍትሄ የሚያገኙት በራሳቸው የጋራ ትግል መሆኑንም እንገነዘባለን።“ከአባብ እንቁላል የዶሮ ጫጩት አይፈለፈልም!”ሁሉም ለእናት አገር ዘብ ይቁም!

**ልዑል ቀስቅስ**
**የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ ተወካይና**
**የዓለምአቀፍ ሊቀመንበር**
**Leul Keskes**
**EPPFG representative & International relations chairman**

አይደለም።አነግ ውስጥ ለውጥ እንዳይመጣ ቀፍድዶ የያዘን ችግር ነው ብለንም እናምናለን።የቅኝ ግዛትና የመሳሰሉት ጥያቄዎች ለህዝባችን ትግል ወሳኝነት የላቸውም።የግፉን ዘመን እየቆጠርን አሁን ያለው ሰቆቃ የሚያጥርበትን ሁኔታ ካላመቻቸን በታሪክ መኖር አንችልም።እስካሁን የተገኙትን ድሎች አቅበን ከሌላው ህዝብ ጋር ተደጋግፈን ወደ ቀጣዩ ትግል መሄድ ነው ያለብን።

**ጥላ:-** ለኢትዮጵያ ዛሬ መረጃ መረብ በሰጡት አስተያየት አነግ የጠራ አመለካከትና ራዕይ አልነበረውም አሁን ግን ሁሉ ነገር ግልፅ ሆኗል ብለዋል። ለምን ነበር የጠራ አመለካከትና ራዕይ ሳይኖራችሁ ከ40 ዓመት በላይ የቆያችሁት?

**አቶ አሚን:-** የአመለካከት ችግሩ መነሻ ሁለት አመለካከቶች በአንድ ላይ ሆነው መሄዳቸው ነበር።የህዝቦችን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ለማስከበር በሚለው አመላካከት ስር ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር አብሮ መኖርና ኦሮሚያን ከኢትዮጵያ መገንጠል የሚሉት አስተሳሰቦች አብረው መሄዳቸው ነበር ለአመለካከት ጥራት ችግር አነግን የዳረገው።እነዚህ የተቀላቀሉ አመለካከቶች ናቸው ትግሉን አጓተውት የቆዩት።አሁን ግን እኛ ያደረግነው ነገር ቢኖር ሁለት የነበረውን አመለካከት በምናምነውና ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በአንዲት ኢትዮጵያ ውስጥ አብረን እንኖራለን የሚለውን ግልፅ አቋም መውሰዳችን ነው።

**ጥላ:-** የፕሮግራም ለውጥ ለማድረግ መብቱም ሆነ ሞራሉ ያለው ህጋዊ አግባብነቱን ያሚላ ጠቅላላ ጉባኤ/ Gumii Sabaa/ ማዕከላዊ ኮሚቴው/ብቻ ነው በማለት የእነ ዳውድ ኢብሳ ቡድን ለሚያነሳው ክስ መከላከያዎ ምንድን ነው?

**አቶ አሚን:-** የእኛ ትኩረት ወያኔ ነው!እንደ ጥያቄ ከተነሳ ግን ከእነዳውድ ኢብሳ ጋር ከተለያየን አራት ዓመታችን ነው።የራሳችን ማዕከላዊ ኮሚቴ፤ወታደራዊ ሃይል፤ካድሬና አደረጃጀት መስርተን እየተንቀሳቀስን ነው።ስለራሳቸው ብቻ መናገር አለባቸው።ነገር ግን ውሳኔው ላይ ከመድረሳችን በፊት ማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎችን/Social Medias/ በመጠቀም ጭምር ብሄራዊ ኮንግረንስ ተደርጎ ነበር፤የኦሮሚያ ምሁራንም ሃሳብ ተካቶ ከቀረበና ሁለት ቀን የፈጀ ውይይት ከተካሄደ በሁዋላ ኮንግረንሱ በጉዳዩ ላይ እንዲወስን ለማዕከላዊ ኮሚቴው/ Gumii Sabba/ሙሉ ስልጣን ሰጠው።በሁዋላም ሜኒሶታ ላይ ባደረግነው ህዝባዊ ስብሰባ ውሳኔአችንን ይፋ አደረግነው።እንደው ከተነሳ አይቀር ተገቢው መልስ መስጠት ስላለበት ነው እንጂ ከተጠቀሱት ሰዎች ጋር አንድ አይነት ባንዲራና አርማን ከመጠቀም ባሻገር የሚያገናኘን ነገር የለም።



**ጥላ:-** ለውጥ አራማጅ ነኝ የሚለውን የእናንተን ወገን የአቢሲኒያዊ ድርጅት ወይም የአማራ ተለጣፊ አድርጎም የእነ ዳውድ ኢብሳ ቡድን ይተቻል።ምንድን ነው ምላሻችሁ?

**አቶ አሚን:-** የኢትዮጵያ ህዝብ ላልባሌና ለፕሮፓጋንዳ የሚያጠፋው ጊዜ የለም። ፕሮፓጋንዳ በቀላሉ የሚሰራጭበት ዘመን አልፏል። ድርጅታችን እስካሁን ድረስ ከግንቦት ሰባትም ይሁን ከማንም ጋር የተፈራረመው ውል የለም።የእነሱ አመለካከት ያመጣው ለውጥ ስለሌለ ስም ማጥፋቱን በመሳሪያነት እየተጠቀሙበት ያሉ ይመስለኛል። የኢትዮጵያ ህዝብ አሁንም ለተልካሻ ምክንያት ቦታ የሚሰጥ አይመስለኝም።የእነ ዳውድ ቡድን ካድሬዎች ጉዳዩን ቢያጣጥሉትም ምሁሩና ህዝቡ ቆየ እንጂ ውሳኔያችን ጥሩ መሆኑን እየገለፁ ናቸው።

**ጥላ:-** ከሌሎች ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በጋራ ለመስራት እንደምትፈልጉ ሁሉ ከእነ ዳውድ ኢብሳ ጋርም መረዳዳት ለመፍጠር ሞክራችሁዋል?ወይስ የታቀደ ነገር አለ?

**አቶ አሚን:-** በትክክልም አለ።እኛ እንኳንስ አብረናቸው ቆይተን ከተለያየናቸው የትግል ጓዶች ይቅርና በአመለካከታቸው ከተለየናቸው የኢትዮጵያ ሃይሎችም ጋር ቢሆን አብረን ለመስራት ጥሪ አቅርበናል።የኦሮሞ ችግር ከኢትዮጵያ ችግር ጋር አብሮ ይፈታል።ስለዚህ በባህላችንም መሰረት ከእነ ዳውድ ቡድን ጋር እርቅም ለመፍጠር ጥረት አድርገናል አልተሳካም።ሁሉንም ነገር ፍርዱን ለኦሮሞ ህዝብ ትተናል።

**ጥላ:-** በመጨረሻም ይህን ቃለመጠይቅ ለማድረግ ስዘጋጅ የኢትዮጵያ መንግስት ደጋፊ ከሆነው አይጋ ፎረም ላይ

## የጋራ ትግል፤ የጋራ አገር!

በጀነራል ከማል ገልቹ የሚመራው አነግ በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ስር ከሌሎች የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ጋር ተባብሮ ለመታገል መወሰኑን ገሃድ አድርጓል።በዚህ ውሳኔ ሳቢያም በኢትዮጵያ የሰፈነውን ዘረኛ አምባገነን ስርዓት አስወግደን በምትኩ የግልና የወል መብቶች የተከበሩባት ፍትህና እኩልነት የሰፈነባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመፍጠር በምናደርገው ትግል ውስጥ አነግ አዎንታዊ የሆነ ወሳኝ ሚና እንዲኖረው የሚያደርግ አዲስ ሁኔታ ተፈጥሯል።

ግንቦት 7 የፍትህ የነፃነትና የእኩልነት ንቅናቄ አነግ በወሰደው አቋም የተሰማውን ደስታ ይገልፃል።በጋራ ትግል የጋራ ጠላታችንን አስወግደን የጋራ አገራችንን ተባብረን እንገነባለን! የሚል ብሩህ ተስፋም ፈንጥቋልናል።

ግንቦት 7 ይህን ለሁላችንም እጅግ አስፈላጊና ፋና ወጊ የሆነውን ውሳኔ የመስጠት አርቆ አሳቢነትና ድፍረት ላገኙት የአነግ የአመራር አካላት ያለውን አድናቆት ይገልፃል።

**ግንቦት 7 የፍትህ የነፃነትና የእኩልነት ንቅናቄ!**



አዲሱ ኦነግ እየተሽከረከረ ያለው በሻዕቢያና በግንቦት ሰባት ነው የሚል ትችት ተሰንዝሮባችሁዋል።ይሄ ደግሞ የመንግስት አቋም እንደሆነ ይገመታል።መልሶ ምን ይሆናል?

**አቶ አሚን:-** ወያኔ ኢህአዴግን ከሁሉም በላይ አሁን ያለበትን የተደላደለ የኢትዮጵያ መሪነቱን የሚያናጋው አሁን የደረስንበት ውሳኔ ነው።ወያኔ ተመቻችቶ ተደራጅቶ ቁጭ ብሏል።ወያኔን ለመጣል ያልተሞከረው መንገድ ቢኖር አሁን የደረስንበት ውሳኔ ነው።በተለይ አማራና ኦሮሞን ሆድና ጀርባ አድርጎ የዘላለም ጠላቶች አድርጎ አስቀምጦ ሲንቀሳቀስ ነበር።ኦነግንም ለውጥ የማያመጣ ግትር / rigid/ አድርጎ ነበር ወያኔ ተደላድሎ የኖረው።ውሳኔያችን ወያኔን ከማንም በላይ ያናጋል።ወያኔ የተለያዩ ምክንያቶችን እየፈጠረ ከኤርትራና ከግንቦት ሰባት ጋር ሊያጣላን እየሞከረ እንደሆነ እናውቃለን።ግንቦት ሰባት የትግል አጋራችን ነው።አሁን የደረስንበት ውሳኔ በማንም ተፅዕኖ የመጣ አይደለም።ማንም ድርጅት ይሁን ቡድን ሊያሽከረክረን አይችልም።ውሳኔው በራሳችን ጀግንነት የደረስንበት እንጂ ማንንም ለማስደሰት ያደረግነው አይደለም።

**ጥላ:-** እንደ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር /ኢሕአግ/ የመሳሰሉ ድርጅቶች ከሻዕቢያ ጋር አብሮ መስራት ከንቱ ድካምና የአገሪቱን ሉኣላዊ ጥቅም ማስደፈር ነው በሚል ትግሉን በአገር ቤት እናካሂዳለን። ኤርትራንም ለቀን ወጥተናል ሲሉ ይደመጣል የኦነግ ከሻዕቢያ ጋር በጋራ መስራት ነገ ችግር ያመጣል ለሚሉ ወገኖችስ ምላሽ ምን ይሆናል?

**አቶ አሚን:-** ችግሩን ስንደርስበት ነው የምናውቀው።እስካሁን ድረስ የኤርትራ መንግስት ማናቸውንም ድጋፍ እያደረገልን ነው።ለእኛ የሚበጀንን ለትግላችን ስኬት አጋር የምንመርጠው እኛ ነን ሰዎች ሊመርጡልን አይችሉም። የኤርትራ መንግስት ለትግላችን እስካሁን ድረስ በጎ ነው።የተለየ አመለካከት ካመጣ ግን ገለልተኛ የማንሆንበት ምክንያት የለም።ለአሁኑ ግን የሚያስፈራ ጉዳይ የለም።የድርጅታችንን ሉዓላዊነት አክብሮ የሚያግዘንን ሁሉ እናከብራለን።

**ጥላ:-** እኔ ጥያቄዬን አበቃሁ። እርሶ ማስተላለፍ ለሚፈልጉት አካል ሁሉ መልእክቶን ማስተላለፍ ይችላሉ። ዕድሉን ሰጥቼዎታለሁ።

**አቶ አሚን:-** በመጀመሪያ ለጥላ መፅሄት ዝግጅት ክፍል ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥታችሁ ለቃለ-ምልልስ ስለጋበዛችሁን ከፍ ያለ ምስጋናን እናቀርባለን።ቀጥዬ ጥሪዬ የሚሆነው ለኦሮሞ ህዝብ ነው።የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ የኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄ መሆኑን በመገንዘብ እስካሁን ድረስ የበደሉንን ይቅር ብለን፤የተጣሉንን ታርቀን፤የናቁንን አክብረን በዛች አገር በጋራ እንድንኖር ጥሪዬን አቀርባለሁ።አሁን የምንከተለው መንገድ የኦሮሞ ህዝብን ሰቆቃ ለማስቆምና የወያኔን ዕድሜ ለማሳጠር ያስችላል።ወያኔን ተደጋግፈን ከስልጣኑ ለማስወገድ እንደ ቀድሞው ሁሉ ከኦሮሞ ህዝብ ብዙ ይጠበቃል።

ለሌሎች ብሄሮችና ብሄረሰቦች የማስተላልፈው መልዕክት ደግሞ አሁን ጥያቄያችን ከኦሮሞ ህዝብ ወደ ኢትዮጵያ ህዝብ ተሸጋግሯል። መላው ህዝብ እኩል እየተቸገረና እየተበዘበዘ በመሆኑ መፍትሄውም መላው ህዝብ በጋራ ተንቀሳቅሶ ትግሉን በአንድነት ሲያካሂድ ይገኛል።አዲሲቷን ኢትዮጵያ ለመገንባት በጋራ እንድንሰራም የአብሮነት ጥሪዬ ይድረሳችሁ።በተለይ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊትና የፖሊስ ሃይሎች አባላትና ኮማንደሮች ታማኝነታችሁ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንጂ የፖለቲካ ቅጥረኛ እንዳትሆኑ ጥሪዬን አቀርባለሁ ። አመሰግናለሁ።

**ጥላ:-** ከ40 ዓመታት በላይ ኦሮሚያ ከኢትዮጵያ መገንጠል አለባት ሲል የነበረው ኦነግ አቋሙን አስተካክሎ ከመላው ኢትዮጵያውያን ጋር በጋራ ለመታገል የደረሰበት ውሳኔ የፈረንጆቹ አዲስ ዓመት ታላቅ ስጦታ እንደሚሆን የመፅሄታችን ዝግጅት ክፍል እምነት ነው። መልካም ዘመን ይሁንልን። እናመሰግናለን።

## ኢህአፓ የኦሮሞን ህዝብ ኢትዮጵያዊነት ተጠራጥሮ አያውቅም!

ኢህአፓ /ዴሞክራሲያዊ/ በጀነራል ከማል ገልቹ የሚመራው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ታህሳስ 22 ቀን 2004 ዓ.ም/ጃንዋሪ 1 2012/ ያወጣውን የአቋም መግለጫ ተመልክቶታል።የአቋም መግለጫው በኢትዮጵያ ውስጥ ለዲሞክራሲ ለእኩልነትና ለህግ የበላይነት በሚደረገው አገራዊ ትግል ላይ በጎ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ብሎም ያምናል።

ኦነግን መሰል ድርጅቶች ከአሁን በፊት ሲከተሉት የነበረውን የመገንጠል ዓላማ ትተውና ኢትዮጵያዊነትን ተቀብለው ጭቆናንና በደልን በማስወገድ በእኩልነት በፍትሃዊነትና በህግ የበላይነት ላይ የተመሰረተች ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ከሚታገሉት ሌሎች ሃይሎች ጋር ትግላቸውን እንዲያስተባብሩ ኢህአፓ /ዴሞክራሲያዊ/ ያለመታከት ላቀረበው ጥሪ ይህ አሁን ኦነግ የደረሰበትና ያወጣው መግለጫ ብሩህ ተስፋ ሰጪና የተባበረ ትግልም እውን ሊሆን እንዲችል የሚረዳ መልካም ፈር ቀዳጅ ነው።

# ደም መፋሰሱ ይብቃ!

**Messeret Kebede/Hanna Nigusse -Arnsberg**

ኢትዮጵያ አገራችንን ወያኔ ማስተዳደር ከጀመረ ጀምሮ በሰበብ አስባቡ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎቻችን በተለያዩ ምክንያቶች ተሰደዋል፤ የደረሱበት ጠፍቷል፤ ለእስርና ለሞት ተዳርገዋል።

በሺዎች የሚቆጠሩም በተለይ በኢትዮ-ኤርትራና በሶማሊያ ጦርነት ተፈጅተዋል። ይህ ሁሉ አልበቃ ያለው የወያኔ መንግስት ይባስ ብሎ አሁንም ተመልሶ ጦራችንን ወደ ሶማሊያ በመላክ ያልተፈለገ ኪሳራ እያደረሰብን ነው።

የአገር ድንበርን ማስጠበቅ ተገቢ ቢሆንም በሰበብ አስባቡ ከጎረቤት አገሮች ጋር በመናከስ የአገሪቱን ዝናና መልካም ስም በማጥፋት ላይ የሚገኘው አምባገነኑ የወያኔ መንግስት ከዚህ ተግባሩ ሊቆጠብ ይገባል።

አገሪቱን ያለወንድ ለማስቀረት የታሰበ በሚመስል መልኩ ልጆቻችንንና ውንድሞቻችንን በተለያዩ የጦር አውድማዎች ለእልቂት እየዳረገ ያለውን ስርዓት በማስወገድ ሰላማዊ መንግስት በአገሪቱ ለመገንባት ሁላችንም የበኩላችንን ማድረግ እንደሚገባን ጥሪዬን አቀርባለሁ። አገራችንን እግዚያብሄር ይባርካት!

# አንድ ኢትዮጵያን እንታደጋት

**Ruth Abebe/Nürnberg**

የሕዝብን አንድነትና ደህንነት ለማስጠበቅ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፍ በመመርጥ ተጠናከረው ጨቋኝ የወያኔ መንግስት እኛ ከአክሱም ስረወ መንግስት የስልጣን ዘመናችን ይፍቀድልናል በማለት እስከአሁን ድረስ ጠብቀን የምንኖር የፖለቲካ ድርጅት ነን በማለት በመንግስታህዊ አገዛዛችን /አስተዳዳራቸው/ የሕዝብን ሰላም በማወክ ህዝብን በጦርነት ለእርሃብ ለኢኮኖሚ መዋዥቅ እንዲሁም የሃገር ህልውናን ለማስደፈር የቆሙ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በአንዱ በኩል እርስ በእርስ አለመስማማትን /የስልጣን ሽኩቻ በመፍጠር በሌላ በኩል ህዝብን ለጦርነት መዳረግ በሌላ በኩል ደግሞ የውስጥ ግንኙነታቸው ሃገርን በአልባሌ ጐዳና ላይ በመጣል የስልጣን ሽፍጠኝነት አካሄዳቸው ሌላው ግድፈት ነው፡፡ አንድ የሆነውን ሕዝብና አንድ ኢትዮጵያን እያወኳት ይገኛሉ፡፡ ይህ ጉዳይ መቀጠል ስለሌለበት መፍትሄው በመላው የኢትዮጵያ ሰፊው ሕዝብ እጅ መሆኑን በመጠቀም በጋራ ትግል የጋራ ለውጥ በአገራችን ለማምጣት የበኩላችንን እንድንወጣ ጥሪዬን አቅርባለሁ፡፡

# ትግላችን ከልብ ይሁን

**ከቢሊሊኝ በነበር/ Bayreuth**

እንደው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስቃይና እንግልት የሚያበቃው ሕዝባችን ከወያኔ ቅጣት ነጻ የሚወጣው በምርጫ ነው ተብሎ ይታመናል? ማነው እና ነው አስመራጩ ማነው ምርጫ ቦርዱ? የተቃዋሚ ድርጅት ተወካይ ታዛቢዎችን ሳይቀር በገንዘብ ለመደራደር ካልሆነም በዛቻ ወይ ማስፈራሪያ የውሸት ውጤት ላይ የሚያስፈርመው ምርጫ ቦርዱ አይደለም እንዴ? ስንት እና ስንት ኢትዮጵያዊ ነው በህዝብ ድምጽ አልቆምርም በማለቱ ቤተሰቡንና ሀገሩን ትቶ የተሰደደው? ታዲያስ ወገኔ በወያኔ አስመራጭነት በወያኔ ታዛቢነት በሚካሄድ ምርጫ ሃገራችን ከወያኔ ቀንበር ነጻ ትወጣለች ብሎ ማሰብ ይቻላልን ወገን ከታገልን ከልባችን እንታገል፡፡

# ከዘላለም ባርነት የአንድ ቀን ነጻነት

**Tigist Alebachew Kassa/Bayreuth**

ውድ አንባቢያን እንኳን ለ2012 አደረሣችሁ፡፡ የዛሬው ጽሁፌ የሚያተኩረው ሀገራችንን ላለፉት 20 አመታት በአምባገነንነትና በዘረኝነት እያስተዳደራት ለሚገኘው ሰው በላ መንግስት ካድሬዎች መልእክት ማስተላለፍ ላይ ይሆናል።

እናንተ የወያኔ ካድሬዎች በተለያዩ ጥቅማጥቅሞት በገንዘብ እና ለግዜያዊ ስልጣን ብላችሁ ወገናችሁን አታሠቃዩ፣ አትግደሉ ይህ አምባገነን መንግስት ዘላለም ስልጣን ላይ አይኖርም በተጠናከረ የሕዝብ ትግል እነ ጋዳፊ፣ ሙባረክ እና ሌሎችም ሲዋረዱ አይተናልና እኛም የኢትዮጵያ ልጆች መለስ ዜናዊና ግብራበሮቹን የምናስወግድበት ግዜ ሩቅ አይሆንም፡፡

እናንተ የወያኔ ካድሬዎች ግዜው ሣያልፍባችሁ የበደላችሁትን ህዝብ ይቅርታ ጠይቃችሁ፣ የሕዝቡን የለውጥ እንቅስቃሴና ትግል ተቀላቀሉ ከዘላለም ባርነት የአንድ ቀን ነጻነት ከፍተኛ የሕሊና ሠላም ይሰጣል፡፡የተባበረ የሕዝብ ትግል ዘወትር አሸናፊ ነው፡፡ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር፡፡

# የኢትዮጵያ መከላከያ ሲፈተሽ

**Tariku Abate/Germany**

ለአንድ ሃገር የዴሞክራሲ እድገት መዳበር ከሚያስፈልጉ መስፈርቶች መካከል ከፖለቲካ ወገንተኝነት የፀዱ ተቋማት አንዱ ነው፡፡ ነገር ግን በኢትዮጵያ እየታየ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ከዚህ በተቃራኒ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ለዚህም ማሣያ የሚሆነንና ሰሞኑን በብሄር ተዋጽኦ በሚል እየታመሰ የሚገኘውን የመከላከያ ሚንስቴር መስሪያ ቤት ማየት በቂ ነው፡፡

በጄነራል ሣሞራ የኑስ

የሚመራውና የኢትዮድያ መከላከያ ሚንስቴር በመባል የሚታወቀው መስሪያ ቤት ገና ከጅምሩ የወያኔ ኢሕአዴግ መንታ ወንድም በመሆን ወታደራዊ ክንፍ ሆኖ ወደሥልጣን የወጣ አካል ሲሆን በተለያየ ጊዜ ወያኔ የፖለቲካ ኪሣራ ውስጥ ሲገባ በጠመንጃ አፈሙዝ እየተወረወረ ከውድቀት የሚታደገው የቁርጥ ቀን ልጅ መሆኑን አስመስክሯል፡፡

በምርጫ 97 በመቶዎቹ ለሚቆጠሩ ዜጐች ሞት ተጠያቂ የሆነው ይህ ሃይል አሁን ደግሞ በምስራቁ የሃገራችን ክፍል ወያኔ እየደረሰበት ላለው ፖለቲካዊ ኪሣራ አጸፋ ለመስጠት ይህው የወያኔ መሣሪያ የታጠቀ ሃይል ግድያና ስቃይ በዜጐቻችን ላይ እያደረሰ ይገኛል፡፡ ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በተሠበሠበ ታክስ የሚንቀሳቀሰው ይህው ቡድን የሃገሪቱን ዳር ድንበር ከማስጠበቅና የዜጐችን ሰላማዊ ኑሮ ከማስጠበቅ ይልቅ የአንድ አነስተኛ ቡድን ስብስብን ጥቅም የሚያስከብር አምባገነን ሃይል በመሆን ላለፈት 20 አመታት በአዲስ አበባ፣ በኦጋዴን፣ በጋንቤላ፣ በጐንደር፤ በአሶሳና በኦሮሚያ የተለያዩ ክፍሎች የአፈናና የግድያ ወንጀል ሲፈጸም ቆይቷል፡፡ ይህ ተቋም ላለፉት 210 አመታት በአንድ ብሄር የበላይነት የተያዘ ከመሆኑም ባሻገር በነዚህ አመታት ውስጥ አንድም ጊዜ ኦዲት ተደርጐ የማያውቅና ለሙስና የተጋለጠ የጥቂት ቡድኖች ስብስብ ነው፡፡

# ሆ ብለን እንነሳ

**ብርሃኑ ባዩ /ሽቫይንፉርት**

ኢትዮጵያዊ ለዘመናት አጥንቱን ከስክሶ ደሙን አፍስሶ ህይወቱን ሰውቶ የገበረላቸው ዋና ዋና መሰረታዊ ጥያቄዎች እስካሁን ድረስ ምላሽ አላገኙም የሃገር አንድነት ዲሞክራሲያዊ ስርአት የመገንባት ፍትህና አስተማማኝ ሰላም ለማምጣትና የሕዝባችን እኩልነትና መብት መከበሩ ቀርቶ ሃገር በዘርና በጐሳ ተገነጣጥላ ለእርስ በርስ እልቂትና እንዲሁም ለሃይማኖት ግጭት ተዳርጋ ትገኛለች፡፡

አሁንም የምንወዳትን አገራችንን እየተውን በስደት አገር ተሰደን ስንገኝ አብዛኞቻችን ለስደት የተዳረግነው በመልካም አስተዳደር ጉድለትና አንባገነኑ የወያኔ አስተዳደር ባደረሰብን ግፍና ጭቆና መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ምኞታችን ኢትዮጵያን በፍቅርና በአንድነት የታነፀች አገር ማየት ነው፡፡ የሁላችንም አላማና ግብ በዘር በሃይማኖት በመደብ ያልተከፋፈለች የህግ የበላይነት የሰፈነባት የሰው ልጅ ስብእናው የሚከበርባት ኢትዮጵያን ማየት ነው፡፡ ይኸው ሁላችንም የምናስባት ኢትዮጵያ በቀላሉ በጥቂቶች ጥረት ብቻ ወይም በዝምታ በምኞት አትገኝም አንዳንዶች እንደሚያስቡት የመለስ ዜናዊ ስጦታ አደለችም ይኸችን የምንነናፍቃትን ኢትዮጵያን ለማየት አስፈላጊ የሆነ መስዋት ሁሉ መከፈል አለበት ኢትዮጵያን እንድትኖር የማይፈልጉና የግል ጥቅማቸው የሚነካባቸው ጥቂት ግለሰቦች እኛ እንዳንቀሳቀስ ተስፋ እንድንቆርጥ እንድንከፋፈል ለማድረግ መሯሯጣቸው አይቀሬ ስለሆነ የምንፈልጋትን ኢትዮጵያን ለማየት የእነዚህን አስነዋሪ ሴራ ማክሸፍ ግድ ይለናል፡፡

ስለዚህ የአምባገነኑን ስርአት ግፍ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ ውድ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ሃገራችንን ከአንባገነኑ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ለማላቀቅ ሆ ብለን እንነሳ፡፡ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

# የታሪክ አሻራ ሲጠፋ በዘረኞች

**Eden Abebe Masresha /Erlangen**

ከፍጥረታት ሁሉ የበላይና ልዩ ክብርና ቦታ ያለው የሰው ዘር መገኛ የሆነችው ውድ እናት አገራችን ኢትዩጵያ ጥንታዊ ታሪክ ያላት በታሪክ ሙሁራን ዘንድ የምትወሳና በስልጣኔ ረገድም ከቀድሞዎች ጋር የምትሰለፍ ሃገር መሆኗ ለማንም ግልጽ ነው፡፡

ታዲያ ዛሬ ዛሬ፣ ጥንታዊ ታሪክ ሣይሆን ስለ ሀገራችን የሚዘከረው በዘር፣ በጐሣ፣ በሃይማኖት የተከፋፈለች ሃገር ለመባል ምንም በገሃድ ባይጠራም በረሃብተኝነት የተፈረጀች ሀገር ከመባል አልፋ የዘረኞችና የአንባገነኖች መዲና ሆናለች፡፡

ታሪክ ከጥንት ሲዘክርና ሲወርድ ሲወራረድ የመጣውን የአባቶቻችን ታሪክ አንድነቷ ተጠብቆ፣ በዘርና በጐሣ ሳይለያይ አንድነቷና ባንዲራችንን ጠብቀው ያቆያትን የአባቶቻችን ታሪክና አጽም ከመቃብ በላይ ከፍ ብሎ ጩኸቱን እያሰማ ይገኛል፡፡

ወያኔ የስልጣን ግዜው ማብቂያውን በ1997 ምርጫ መጠናቀቁን ሲረዳ ህብረተሰቡን በዘር፣ በሃይማኖት፣ በጐሣ ከመከፋፈሉም ባሻገር ሀገሪቱን በኢኮኖሚ በማድቀቅ ላይ ይገኛል ዛሬ ፎረም ብሎ የራሱን የፖለቲካ አራማጆች እንደ አሸን በማፍላት በየቀበሌውና በየመንግስት መስሪያ ቤቶች በማጐር ሠላማዊን ህዝብ ሲያምሠው የሚመለከት ህሊና የሌለው እሱን በሠላማዊ መንገድ ሲፋለመው በታማኝ ወታደሮቹ ደግሞ ከ9 አመት ህጻን እስከ አረጋዊያን የጥይት ራት የሆኑበት ግዜ የቅርብ ግዜ ትዝታዎችም እንዳሉ በእሳት ውስጥ እየተገፈ ቤት ይቁጠረው ማን ይናገር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ ነው ብሂሉ፡፡

ወገኖች ጥንት አባቶቻችን ሲተርቱ የቸገረው እርግዝ ያገባል ይሉ ነበር አሁን ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር የወያኔ ፎረም ሆኖ ማገለገልና ባርነነትን መምረጥ የግድ ሆኗል፡፡ እስከ መቼ ሠው ሆነን መፈጠራችንን ረስተን እንባ ጠባቂ ሆነን እያጐበደድን እንኖራለን ብንሞት አይሻለንምን?

አሁን አሁንም ሀገራችን ሰላም ናት ግንባታውን ተያይዘነዋል እርዱን ለግንባታ በማለት በዲያስፖራው እና በአውሮፖው አለም ማጭበርበሩ ተያይዞታል፡፡ የግንባታው ብር ግን በአግባቡ እየዋለ ሣይሆን የህብረተሰቡን አሳብ እና አመለካከቱን ለመቀየር እያደረገ ያለው ስልቱ የሃገሪቱን ኢኮኖሚ ያለመመጣጠን የኑሮ ውድነት ያሠቃየውን ህዝብ የማታለያ ስልቱን ልብ ልንል ይገባል፡፡

# ወያኔዎች የተንኮል ጉድጓድ አትቆፍሩ የሚገባበት አይታወቅምና

**Arsema Yonas /Erlangen**

የኢትዮጵያ ህዝብ የዲሞክራሲ መብት ሊከበር ነው ተብሎ ዲሞክራሲያዊ መፈክሮች በማየቱ ዲሞክራሲ የጠማው የኢትዮጵያ ህዝብ በእልልታ ታጅቦ ነበር ነገር ግን የኢስሙላህ ዲሞክራሲ መሆኑን ከበስተጀርባው የያዘው አላማ ኢትዮጵያን በመበታተን ህዝቦችን በጐሣ፣ በዘር፣ በሃይማኖት በመከፋፈል እርስ በእርሱ አጋጭቶ ለ20 አመታት የስልጣን ዙፋኑን በመያዝ ህብረተሰቡን ከፋፍሎታል፡፡ ለዚህ አብይ ምስክሩ ዜጐች የዜግነት ግዴታቸው ተወጥተው ያቆዩትን የኢትዮጵያ ሠንደቅ አላማ ባንደራችንን ጨርቅ ነው ብሎ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ መነገሩ እንደውስጥ እግር እሳት እያቃጠለን ይገኛል፡፡ ጀግኖች አባቶቻችን ወንድሞቻችን እንስት እህቶቻችን ጥንት አጥንታቸውን አድቀው ደማቸውን አፍሰው ያቆዩትን ክብራችንን ዝግ አድርጐ መናገር ንቀት መሆኑን ማንም ሊገነዘበው ይገባል፡፡

ይህ ንቀታቸው ከ1997 ኢ.ም ጀምሮ ብሶት የወለደው የኢትዩጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ያቀጣጠሉትን ህዝባዊ አመጽ በወያኔ ጋሻ ጃግሬዎችና ሎሌዎች ቢያዳፍኑትም ጨርሶ ግን አይጠፋም አመድ የለበሰ እሳት ውስጡ እረመጥ እንዳለው ወያኔ እራሱ ሊረዳው ይችላል፡፡

ዛሬ አለም በአንድ የፖለቲካ ጐራ ውስጥ ተሠባስቦ ስለ አገር ለውጥና ኢኮኖሚ እያሰበ ባለበት ወቅት የኢትዮጵያን ህዝብ በዘር በሃይማኖት ከፋፍሎ በብሄር ብሄረሰቦች ስም በመነገድ ሃገሪቱን ወደማትወጣው አዘቅት ለመጨመር የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ባንዴራ በማስያዝ በ11 ክልል ከፋፍሎ የባንዴራውን ቁጥር አብዝቶ ዜጐች እርስ በእርሳቸው ተከፋፍለው የጦርነት እሳት እንዲጭሩ አስደርጓል ለአብነት በደቡብ ክልል የተከሰተው የሃይማኖት መከፋፈል በጅማ፣ በአዲስ አበባ በአየር ጤና እና፣ በመርካቶ እንደሁም በጐንደር እየደረሰ ያለው የስልጣን ጥም ማራዘሚያው አብይ ሲሆኑ በኢኮኖሚ ደረጃ የሃገርን አንጡራ ሃብት የሆነው ወርቅ ማህድን መሸጥ ለም መሬትን ለአበባ መተክያ ሰበብ በሊዝ መሸጥ የአርሶ አደሩ ንብረት የሆነውን መሸጡ ሣያንሰው የግጦሽ መሬት አሳጥቶ ህብረተሰቡን ለድህነት እያዳረገው ይገኛል፡፡

የታሪክ ተወቃሽ ሆኖ ለትውልድ የማይሸር ጠባሣን መተው የህሊና እዳ ነውና እዳ ያለባችሁ ለመክፈል ልትጥሩ ይገባችሃል፡፡ አልያ ግን አይቀጡ ቅጣት ሊመጣ ይችላልና ልንጠነቀቅ ይገባል ምክንያቱም አበው ሲተርቱ የተንኮል ጉድጓድ አትቆፍር ኋላ የሚገባበት አይታወቅምና ይላሉ እና ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ እላለሁ ወዳጆች፡፡

# አምባገነኑ የወያኔ መንግስት

**Siraye Tadele/Erlangen**

አምባገነኑ ደርግ በነበረበት ጊዜ እንዲሁም የሃገር ውስጥ ጭፍጨፋ እና እንደሁም በሶሻሊዝም የሚመራው ከዛም አልፎ ወታደራዊ አመራር ዲሞክራሲ ፈጽሞ የማያውቀውን አንባገነኑን ደርግ በ1983 ግንቦት 20 የወያኔ መንግስት ሲገረስሰው የኢትዮጵያ ብሄር እና ብሄረሰቦች በደስታ ተቀበሉት በተለይ የወንድ ልጅ እናቶች ደርግ ልጆቻቸውን በማዝመት ሲያሰቃያቸው ስለነበር የሆነው ሆኖ እንግዲህ አምባነነኖች ታላቋን ኢትዮጵያ ተቆጣጠሩ ጥራት እና ትግል ቀስ እያለ ነው፡፡ እንደሚባለው ሁሉ ቀስ በቀስ እዝባ ኪዳን ወደ ማኛ እንደገባ ተለላ ዘረኛው የወያኔ መንግስት ሀ ብሎ ጥፋቱን ጀመረ። ዘረኛ መንግስት የማንነታችንን ማንነት የሆነው ከትውልድ ወደ ትውልድ የተሻገረውን አባቶቻችን ደማቸውን አፍሰው አንድ ያደረጓትን ሀገራችንን ነጻ ያወጡልን የብዙ የሃገሬ ሰው የባንድራ ፍቅር ተቀብሮ እንደቀራ ምስል አደረገ እንዲ በማለት ባዲራ ጨርቅ ነው እኛ የምንፈልገው ልማት ነው እያለ በብዙሀን መገናኛ አወጀ ይህንን የሰማው የኢትዮጵያ ልጅ ጩኸቱን አሰማ ነገር ግን የህዝብ ጩኸት ለመንግስቱ ቀልድ ቢሆንም የወያኔ መንግስት እያጭበረበረ ህዝብን እያታለለ ዛሬ የባንዲራ ቀን ተብሎ ኢትዮጵያ ውስጥ መከበር ተጀምሯል፡፡

የወያኔ መንግስት ህዝብን ለማስተዳደር ሳይሆን ኢትዮጵያ ሃገራችንን ለመከፋፈል በዘር በሃይማኖት በቀለማት ሃገራችን ለመጥፋት ቆርጦ የተነሳ አንባገነን መንግስት ነው፡፡

# ኢህአዴግ እና አደገኛ ስትራቴጂው

**Eden Dawit /Gießen**

በአንድ አገር ውስጥ ሠዎች በሰላም ለመኖር እናም በአገራቸው ጉዳይ ላይ በጋራ እኩል ለመመካከር የሚችሉት በአገራቸው ሠላም እና መረጋጋት ሲኖር ብቻ ነው፡፡ በአሁኑ ግዜ በአገራችን በኢትዮጵያ እየተፈጸመ ያለው አደገኛ ሁኔታ ቀላል የሚባል አይደለም ሕዝብን ከህዝብ ጋር በማጋጨት የስልጣን ጊዜያቸውን ሊያራዝሙ በሚፈልጉ ስግብግብ ባለስልጣናት ተዋጅና ተሳስቦ ይኖር የነበረውን ሕዝብ እንደ አውሬ በማባላት ላይ ይገኛሉ፡፡ የሕዝባችን የእለት ተእለት ኑሮ ሠላም በማጣት እና ዛሬ ምን ይፈጠር ይሆን እያለ በስጋት እንዲኖር ተገዷል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድ ጐን የኑሮ ውድነት መሄጃና መቀመጫ ሲያሳጣው በሌላ በኩል የመኖር ህልውናው ጥያቄ ውስጥ እንደሆነ ይታየዋል፡፡ ምክንያቱም በአገራችን ኢትዮጵያ እየተደረገ ያለው ወንድም በወንድሙ ላይ መነሳቱ በእምነቱ ተከፋፍሎ የማያውቀው ህዝብ ሙስሊም ክርስቲያን በመባባል ጐሳ በመለያየት መጣላቱ መገዳደሉ በርክቶ መታየቱ የተለመደና ፍጻሜውም ምን ላይ እንደሆነ ሁከት አስጀማሪዎቹም ባለስልጣኖቻችን የማያውቁት አይመስለኝም ይህ አደገኛ መንገድ ምን ያሕል ሕዝቦችን ለከፋ እልቂት

እንደሚደረግ የወያኔ ባለስልጣኖች እንዴት ጠፉቸው? ወገኖቼ ታዲያ ከኛ ምን ይጠበቃል? ለሕዝባችን ምን እያደረግን ነው ወሳኝ ጊዜ ነው እና እባካችሁ አንዲነታችንን አጠንክረን ይህንን አረመኔና የሠላም ጠር የሆነውን የወያኔ መንግስት ለማስወገድ በአንድ እንነሣ እግዚአብሄር ከኛ ጋር ይሁን፡፡እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ!

# ሁሉም ይንቃ

MEKDES BERHANU /FRANKFURT/

ኢ-ዲሞክራሲያዊው ወያኔ ስልጣኑን ለማራዘም ከሚጠቀምባቸው ዘዴዎች ውስጥ ሃይል አንዱ ሲሆን ሌላው -ደግሞ ሕዝቡን በተለያየ መንገድ በመከፋፈል እርስ በርሱ እንዳይግባባ እና እንዳይተማመን በዘር መከፋፈልና ማጋጨት ዋነኞቹ ናቸው፡፡

ጸረ ሕዝቡ ወያኔ በቅርቡ እያደረገ ያለው ሌላኛው ህዝብን የመከፋፈያ ዘዴ ደግሞ በተለያዩ አገሮች የሚገኙ ኢትዮጵያውንን በጥቅም መሸንገል ነው፡፡

ይኸውም ከኢሕአዴግ ጋር የተስማማውን ሀገር ቤት የቤት መስሪያ ቦታ በመስጠት እንዲሁም ወደ አገር ቤት ገብተው የቅንጦት በአላትን እንዲያከብሩ መገፋፋትን እና በሱ ላይ ተቃውሞ የሚያሰሙትን በይስሙላ ጥቅማ ጥቅም በመደለል በውጪ ሃገር የሚደረግበትን ጫና ለመቀነስ እየተራወጠ ነው፡፡

የሃገራችን ምስኪን ጥሩ በልቶና ጥሩ ለብሶ እንዲያድር ማድረግ ያልቻለ መንግስት ከኔ ጋር ካበራቹ ይሕንን ጥቅማ ጥቅም ታገኛላችሁ እያለ በውጭ ሀገር ላሉ ኢትዮጵያውያን የሚደሰኩረው ደስ ብሎን ሳይሆን በዙሪያ ጥምጥም ራሱን ለመጥቀም እንደሆነ ሁላችንም ተረድተን በአምባገነኑ ወያኔ ላይ የምናደርገውን ተቃውሞ ሁላችንም በመተባበር እንቀጥል፡፡ድር ቢያብር አንበሳ ያስር ነውና ብሂሉ በአገር ውስጥም ይሁን በውጭ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን የወያኔን የአገዛዝ ዕድሜ ለማሳጠር የሚጠበቅብንን ሃላፊነት ለመወጣት ቆርጠን እንድንነሳም ጥሪዬን አቀርባለሁ።

# የማሕበራዊ ድሕረ ገጾች ፖለቲካዊ ፋይዳ

**Abinet Belay/ Kronach**

ባለፈው የፈረንጆች ዓመት ዓለምን ሲያነጋግር የከረመው የምእራብ አፍሪካ እና የአረቡ አለም ፖለቲካ በማህበራዊ ድህረ ገጽ በመታገዝ፣ በአምባገነን መንግስታት ላይ ያመጣው ለውጥ ነው፡፡

ይህ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ከቱኒስ ተነስቶ የግብጽን አምባገነን ስርአት ገርስሶ ፣ ወደ ሊቢያ ጐራ ብሎ የጋዳፊን የ42 ዓመታት የጃጀን ስርአት ጦር አስጨብጦ፣ ወደ መካከለኛው ምስራቅ ጐራ ብሎ የሳውዲ፣ ባህሬን እና የመንን መሪዎች ልባቸውን አርዶ አሁን ሙሉ ጓዙን ጠቅልሎ ከሶሪያ ከትሟል፡፡

በዚህ ለውጥ ውስጥ ትልቁ የመረጃ መለዋወጫ ሆኖ የከረመው የማህበራዊ ድህረ ገጽ (Social Network) ነው፡፡ ፌስ ቡክ (Facebook) እና ትዊተር (Twiter) ዋነኞቹ የመረጃ መለዋወጫ እና የአቢዮቱ ቀስቃሾች ሆነው ሰንብተዋል፡፡ የነዚህ ድህረ ገጾች አቅምም በአስደናቂ ሁኔታ ለለውጡ አስተዋጽዎ አበርክተዋል፡፡

በአሁን ሰአት በሃገራችን እየተደረጉ ያሉ መሰል እንቅስቃሴዎችንም እንደ አንድ ትልቅ እና ዋነኛ የመረጃ ምንጭ አድርገን እየተጠቀምን ያለነው እነዚህን የማህበራዊ የመረጃ መረቦች ነው፡፡ ምንም እንኳን የወያኔ መንግስት ትልልቅ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የፖለቲካ ድሕረ ገጾችን መረጃዎች ለሕዝቡ እንዳያስተላልፉ ቢገድባቸውም እኛ በውጭው አለም በስደት የምንኖር ኢትዮጵያዊያን በሀገር ውስጥ ካሉት የተሻለ ነጻነት እና እንኚን የመረጃ ምንጮችን የመጠቀም እድሉ ስላለን፣ በሃገር ውስጥ እንዳይተላለፍ የተገደቡን የፖለቲካ ድሕረ ገጾችን ዜናዎች እና መረጃዎችን ወደ ማሕበራዊ ድህረ ገጾች በማስተላለፍ ፣ መረጃዎች ለህብረተሰቡ በተገቢው ሁኔታ እንዲደርሱ ጥረት ማድረግ አለብን፡፡

እንደ ኢትዮ ሚዲያ (Ethio Media) ፣ ኢትዮጵያን ሪቪው (Ethiopian Review)፣ ናዝሬት (Nathret.com) እና መሰል የመረጃ መረቦች የሚያወጡትን ዜናዎች በፌስቡክ እና ትዊተር እንዲሁም በግል ኢሜሎች በማሰራጨት፣ ሃገር ውስጥ ላለው ሕዝብ ማቀበል አለብን፡፡ ከመረጃ ባሻገር ቅስቀሳዎችን እና ፖለቲካዊ መማማርን በማሕበራዊ ድረገጾች ማዳበር ለምናደርገው ትግል ትልቅ አስተዋጽዋ አለው፡፡

እነኚን ከዘመን የተጣሉ ጠባብ ብሄርተኞች በሀገራችን ላይ ተጣብቀው የሚኖሩበትን ጊዜ በትግላችን አሳጥረን መርዘማው አመራራቸውን እናረክሰዋለን፡፡

# መታገል አለብን

Alemayhu Minwuyelet /Schweinfurt/

በወያኔ /ኢሕአዴግ/ መንግስት ያለፉት ሃያ ዓመታት ሕዝቦቿን በዘር እንዲለያዩና እርስ በእርሳቸው እንዲጣሉ የወያኔ መንግስት በዘረኝነትና በማን አለብኝነት ወገንን በጐጥ እያለያዩ የእርስ በእርስ ጥላቻንና ቁርሾን በመንዛት ብሎም ሕዝብን በማጋጨት የሃገርን አንድነት ስሜት እየሸረሸሩ ያሉት ጠባብ ብሄርተኛ ቡድኖች ፈጽም የሃገሪቱን አንድነት ስሜት ሊጠብቁ አይችሉም፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ይሕንን ሁኔታ ለመለወጥ በምትኩም ሃገራዊ አንድነትና ሉአላዊነቱን ጠብቆ በፍትህ በዲሞክራሲያዊ በእኩልነት ተፋቅሮና ተቻችሎ ለመኖር ከደም ጠብታ እስከ ነፍስ መስጠት መታገል አለብን፡፡

ስለዚህ በውጭ ሃገር የምንኖር ኢትዮጵያን የአቅማችንን ገንዘብ በማሰባሰብ በሞራል እና በመሣሡሉት በመረዳት ሁላችንም በጋራ የጋራ ጠላታችንን ኢሕአዴግ /ወያኔ/ መንግስት ጦርነት ልናውጅበት ጊዜው አሁን ነው ይሕን በትክክል ተረድተን ከአርበኞች ግንባር ጎን እንቁም እላለሁ፡፡ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

# ግዜው ቅርብ ነው

**Yosef Kifle /Germering**

በቅርብ ጊዜ ውስጥ በአለም ላይ በጣም አስገራሚ የሆኑ ለውጦች ታይተዋል፡፡ ከነዚሕም በቱኒዝያ፣ በግብጽ፣ እንዲሁም በሊቢያ የማያዳግም የአንባገነኖች ውድቀትን መላው አለም በአግርሞት ሲከታተላቸው ቆይቶአል፡፡

በተለይ የሊቢያው መሪ የነበሩት ሙአመር ጋዳፊ የግፍ መጨረሻ ከፍተኛ ትምህርት ሰጥቶ አልፎአል፡፡ ይሁንና አሁንም በአለም ላይ ያሉ የተለያዩ አምባገነን መሪዎች ለምሣሌ እንደ ሶሪያው አልአሣድ፣ የየመኑ አሊ ሣላህ አብደላ፣ የሻቢያው ኢሣያስ አፈወርቄ፣ እና የኛው መለስ ዜናዊ አሁንም የአልሞት ባይ ተጋድሎአቸውን ተያይዘውታል፡፡ በተለይ የኢትዮጵያው መለስ ዜናዊ በተለያየ ጊዜ የተለያዩ አፋኝ ህጐችን በማውጣት እንደ የፕሬስ ህግ፣ የሽብርተኛ ህግ፣ የእርዳታ ድርጅቶችን የተመለከተ ህግ፣ አሁን ደግሞ የመሬት ይዞታ ህግ አውጥቶ ህዝባችንን እያመሰው ይገኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተለያዩ አደናጋሪ አጀንዳዎችና ፕሮግራሞችን ለምሣሌ የአባይን ወንዝ እገድባለሁ በማለት፣ በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ ሠፋፊ መሬቶችን ለውጭ ሃገር ባለሃብቶች በመሸጥ ላይ ይገኛል፡፡ ይሄንን የሚያደርገው ሕብረተሰቡን ለመከፋፈል እና እድሜውን ለማራዘም ነው፡፡

በተጓዳኝም በሠላማዊ መንገድ በ2002 ምርጫ ላይ ተሣትፈው የነበሩ ከፍተኛ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች አመራሮችንና አባሎችን እንዲሁም ተቃዋሚ ግለሰቦችን እንኳን ሣይቀር እያሠረ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት ኢኮኖሚያችን አድጐአል ከግብርና መሪ ወደ ኢንዱስትሪ መሪ ተሸጋግሬአለሁ ባለበት ወቅት አለም እንደሚያውቀው ከ12ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ለረሃብና ድርቅ ተጋልጦ ይገኛል፡፡ ይህም የሚያሣየው በሃገሪቱ ውስጥ ያለውን የመልካም አስተዳደር እጦትን ነው፡፡

በመሆኑም ይህንን ጨካኝና አረመኔ መንግስት ከኢትዮጵያና ሕዝብ ጫንቃ ላይ ለማውረድ በውጭም በውስጥም ያለነው ኢትዮጵያዊያን ልዩነቶቻችንን በማቻቻል በአንድነት ሆነንን የምናስወግድበት ጊዜው አሁን በመሆኑ የግፍ አገዛዝ በቃ ብለን ልንነሣ ይገባል፡፡ ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

# ህዝባችንን ልንደርስለት ይገባል

**Amanuel Kiros /Schweinfurt/**

በሀገራችን ላይ ያለው የኢሕአዴግ /መንግስት/ ክፉ ምክር ሲመክር እነሆ ሁለት አስርት ዓመታት ተቆጠረዋል አንዱ ህዝብ ጠላት እንዲሆን ተሰብኳል በህዝብ መካከል ቋሚ ጥላቻን የሚመሰክሩ ሃውልቶችም ቆመዋል አገሪቷ የነበራት እሴቶች ሆን ተብለው በኢሕአዴግ መንግስት በጥናት ተዘምቷባቸዋል።በአገሪቷ ህግ በአንድ ክፉ ጣኦት ስሜት ተተክቶ ፍትህ በመጥፋቷ ዜጐች ለእስራት ተዳርገው ከሚወዱት ህዝብ በመለየትና ተስፋ በመቁረጥ ወደ ሌሎች ዓለማት ሀገሩን ትቶ በመሰደድ ላይ ይገኛል፡፡

ስለዚህ በሀገራችን እየተደረገ ያለውን ኢ-ሰብአዊ ድርጊት ባለንባቸው አገራት ሁሉ በማጋለጥ በእስራት በድብደባ በማስፈራራት ሰበብ በመሰደድ ላይ ያለውን ህዝባችንን ልንደርስለት ይገባል፡፡ ኢትዮጵያን እግዚአብሄር ይባርካት!

# ወያኔ እጁን ከሃይማኖት ተቋማት ላይ ያንሳ!

**Mulugeta Mulatu Hailu/ Germany**

ዛሬም ቢሆን አገራችን ኢትዮጵያ የ3 ሺህ ዓመታት ስልጣኔ ውጤት በአፍሪካ ብቸኛዋ የነጻነት ምንጭ መሆኗ ታሪክ ያስቀመጠው ሃቅ ነው። የዚህች አኩሪና አስደሳች ታሪክ ባለቤት የሆነው ሕዝብም ለነጻነቱና ለሰብአዊ ክብር ሲሉ ትልቅ አስተዋጻ የከፈሉት አባቶቹ በእምነትና በእውቀት የታነፀ ስርአት አውርሰውን እያለ አምባገነኑና ዘመነኛው የወያኔ አገዛዝ በዴሞክራሲ ስም እየተገዘተ በዘር መከፋፈሉ ሳያንስ በእያንዳንዱ የእምነት ተቋማት ላይ ጣልቃ እየገባ እምነታቸውን በሰላም እንዳያራምዱ የፖለቲካው መጠቀሚያ በማድረግ ላይ ያለ የለየለት ከፋፋይ መንግስት ወደመሆን ደረጃ ደርሷል።ለዚህም ቀላሉ ማሳያ እዚሁ ጀርመን ላይ ያሉትን አብያተ-ክርስቲያናት ማየት ይቻላል፡፡ስለሆነም አምባገነኑ የወያኔ ስርዓት እጁን ከሃይማኖትና ከሲቪል ማህበረሰቡ አደረጃጀት ላይ ማንሳት አለበት።ይህ ግን በተደጋጋሚ ቢሞከርም ሊሳካ ባለመቻሉ ያለው ብቸኛው አማራጭ አምባገነኑን ስርዓት ማናቸውንም መንገዶች በመጠቀም ከስልጣኑ ማስወገድ በመሆኑ ሰፊው ህዝብ በጋራ እንዲነሳ ጥሪዬን አቀርባለሁ።ድል ለሰፊው ህዝብ!!!!

# ትግሉን እንቀጥል

**Abiy Getachew/Germany**

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጭቆናና ከብዝበዛ ኑሮ ተላቆ በገዛ ሃገሩ ላይ ነጻና ባለሙብት ሆኖ ለመኖር የሚያስችለው ዴሞክራሲያዊ መንግስት ተቋቁሞ ለሃገሪቱ ዜጋ ተገቢና ሚዛናዊ አስተዳደር ማስፈን የሚችል ሲሆን ብቻ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ባሕሎች በጐ ይዘቶች እየተበላሹ ስፍራቸውን ለቀው ዘረኝነት እየተስፋፋ ነው። በዚህም እንደ እውነቱ ከሆነ ወያኔ ተለውጦ ዴሞክራሲያዊ ወይም በፈቃዱ ስልጣን ይለቃል ማለት ዘበት ነው እናም በተናጠል ሳይሆን በተባበረ ክንድ ጠላትን መምታት ነው፡፡ በንጹህ ኢትዮጵያውያን ደም መታጠብ የለመደ ሕዝብን ረግጦ ሃገሪቱን እየመተረ ለባእድ እየሸጠ ያለው መንግስት የተቀናቃኞች ክፍፍል ጠቅሞት የከበረ ቢመስልም የተባበረ ምት ቢያርፍበት የዛለ እንደሚሆን ግልጽ ነው። አረመኔው መንግስት ኑሮውን ለማደላደል ከመጠን ያለፈ ከዜጐች የተዘረፈ ሃብት ማግኘት ችሏል ይህን የተቃወሙ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሕግ መድረክ በግልጽ እንዳይታገሉ በመታገዳቸው ምላሹ እስርና ጭፍጨፋ በመሆኑ የዴሞክራሲ ትግሉ ሊዳብር አላስቻለውም ጠላታችን ወያኔ በእግረ ሙቅ እያስፈራራ ዝም ብለህ ተገዛ ቢልም በተባበረ ክንዳችን ከገባንበት ባርነት ነጻ መውጫ ጊዜው አሁን ነው እላለሁ፡፡


IF YOUR GOVERNMENT
SHUTS DOWN
THE INTERNET,
SHUT DOWN
YOUR GOVERNMENT.


FREEDOM
OF SPEECH

# የገና ስጦታ

Aberash Belayneh/Kronach

እንኳን ለአውሮፓውያኑ አዲስ አመት በሰላም አደረሣችሁ ብዬ ብል መቼም ዘገየሽ እንደማትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ወገኖቼ አመትስ እንዳለፈው ዘመናት ሁሉ ቁጥሩን ለውጦ አለፈ የሃገር ቤት ፖለቲካ ግን ወያኔን እንቅልፍ እንደነሣው ይኸው አለ፡፡

በያዝነው የፈረንጆቹ ዓመት የኦሮሞ ነጻነት ግንባር /ኦነግ/ ያበረከተልን የገና ስጦታ ከሁሉ የላቀ ነው፡፡ የኦሮሞ ነጻ አውጪው ችግር እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ የዲሞክራሲያዊ እና የሰብአዊ ቀውስ ጉዳይ ነው፣ በሃገራችን እየደረሰ ያለው የአገዛዝ በደል በኦሮሞ ብቻ ሳይሆን በመላው ኢትዮጵያዊ ላይ ነው፤ ስለዚህ ከመላው ኢትዮጵያዊ ጋር በማበር ነጻ የሚያወጣው ኦሮሚያን ብቻ ሣይሆን ኢትዮጵያን ነው የሚል አዲስ ዘመናዊ እና ከሌሎች ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር አንድ የሚያደርግ ሃሣብን እነሆ በረከት ብሏል፡፡ ድንቅ ስጦታ ይሏል ይህ ነው!!!

ባሳለፍነው የአውሮፓውያኑ 2011 የግንቦት 7 እና የኦሮሞ ነጻነት ግንባር የሆነው ኦነግ ባደረጉት የፖለቲካ አስተሳሰብ መወራረስ እና መወያየት ከአንድ ማእከላዊ ከሆነ አቋም በመድረሳቸው እና መላው ኢትዮጵያውያንን አንድ በሚያደርግ አስተሳሰብ ላይ በማተኮራቸው በዘር፣ በሃይማኖት፣ በአስተሳሰብ፣ በሃብት በመሳሰሉት ከፋፋይ የፖለቲካ ስርአትን ለማስወገድ ከስምምነት ላይ ደርሰዋል፡፡

ኦነግም በአዲስ አመት እነሆ በረከት አዲስ አስተሳሰብ ብሏል፡፡ ምንም እንኳ ለኛ ጮቤ ቢያስረግጥም ለወያኔ ግን ትልቅ የራስ ምታት ሆኖታል፡፡ይህንን የተቀደሰ ስጦታ እሰይ ብለን ተቀብለን በያዝነው የፖለቲካ ትግል ውስጥ አንድነታችንን በበለጠ ካጠናከርን በ2012 ከመግቢያው ትግል ውስጥ አንድነታችንን በበለጠ ካጠናከርን በ2012 ከመግቢያው ወያኔን አንድ ለ ባዶ መራነው ማለት አይደል?

# ወያኔ ያተረፈልን

Suzan Mulu Abraham /Nürnberg/

ለ20 ዓመት /ወያኔ/ አገሪቷን ከተቆጣጠራት በኋላ በተግባር ያየነው እሱ እንደሚለው በየአመቱ የ10 እና 11% እድገት ማስመዝገብ ሣይሆን በመጀመሪያ በተላላኪነት ኤርትራን ማስገንጠል አልፎም የባህር በራችንን ማስወሰድ 70 ሺህ የሚሆኑ ኢትዮጵያንን ካስጨረሰ በኋላ የሞትንበትን መሬት ለባላንጣዋ ኤርትራ ማስረከብ ነበር፡፡ አላማችን በማለት ባድሜን መልሶ በህጋዊ መንገድ ለኤርትራ አሣልፎ መሥጠት ከዚያም አልፎ የኢትዮጵያን አርሶ አደር ገበሬ ከቀዬው በማፈናቀል እርሻውንና መኖሪያውን የሱዳን ማድረግ፣ ለኢሲያና ለአረብ ቱጃር በኢንቨስትመንት መልክ ለኢትዮጵያ የሚጠቅመው ነገር ሣይኖር መሸጥ የተማሩትን፣ ጋዜጠኞችንና ተቃዋሚ ሃይላትን ማሠር ማሠቃየትና ከአገር እንዲወጡ ማድረግ የዘወትር ተግባሩ አድርጐታል ስለሆነም ለዚህች አገር ያተረፈው ስደት ረሃብ የአገር መገጠል የጐሣ ግጭትና ጠባብተኝነትን ነው፡፡ በመሆኑም ይህ የወያኔ መሪ መለስ የአገዛዝ ዘመኑ አብቅቶ ለፍርድ ለማቅረብ ሁሉም ኢትዮጵያዊ አንድ መሆን ይጠበቅበታል እላለሁ፡፡ወያኔ ይወገድ!

# ዴሞክራሲን የማያቅ መንግስት በሃይል ይወድቃል!

Yonas Tesfay/Fulda/

ኢትዮጵያን በማፈራረስ ታሪኩ የሚታወቀው ዘረኛው የወያኔ መንግስት ላለፉት 21 አመታት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያደረሰውና አሁንም እያደረሰ ባለውን ስቃይ ዘመን የማይረሳው ስርአት ለመሆን የሚያደርገው የዘረኝነትና የመበታተን አላማ ግልጽ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ፍትሕና ነጻነት የሰፈነባት ሰዎች በዜግነታቸው እኩል የሚታዩበት ዴሞክራሲያዊት ሃገርን ማየት የሚናፍቅ ኢትዮጵያዊ የሆነ ዜጋ ሁሉ አሁን ወሳኝ ፊልሚያ ውስጥ ነን ፍትህና ነጻነት ይገባናል የምንል ከሆነ ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ እንሁን ደሞክራሲ በብዙ ብር የሚገዛ ግኡዝ እቃ አይደለም ውድ የሆነውን የህይወት ዋጋ የሚያስከፍል እንጂ! እውነት ነው ፍትህና ነጻነት ዋጋ ያስከፍላሉ ግን ይህንን ውድ ዋጋ ማን ይክፈለው?

አንድነት ሃይልን ይፈጥራል እንዲሉ እያንዳንዳችን ይህንን ዘረኛ መንግስት ለማስወገድ በአንድነት መነሳት አማራጭ የሌለው መፍትሄ መሆኑን ማወቅ ለትግሉ ወሳኝ እውነታ ነው ግን የትግል ድርሻችንን ወደ ጐን ብለን ትግሉን ለጥቂቶች አሳልፈን ከተውን ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘለአለም የማይጠፋ ጠባሳ ለዘር ትቶ ማለፍ ከሞት በላይ ሞት ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ወያኔ እራሱ ባዘጋጀው የምርጫ ጊዜያት እንኳን የስንቱ ነጻነት ፈላጊ ወጣት ግንባር በወያኔ ቅልብ ጦር ግንባራቸውን እየተመቱ ሞቱ ስንቷ ደሀ እናት ልጇ ተምሮ ይጦረኛል ስትል በራፍ ላይ ወድቆ ቀረ? ምንግዜም ቢሆን የማንረሳው እውነታ ነው ዛሬም ኢትዮጵያን ለማጥፋት ቆርጦ የተነሳው የወያኔ መንግስት አባቶች በክብር የወደቁለትን የኢትዮጵያን ለም መሬት ለሱዳንና ለውጭ ባለሃብቶች በመሸጥ ገበሬውን አፈናቀለ። ለብሄር ብሄረሰቦች መብት ቆሚያለው ያለው ወያኔ አንዱን የአንዱ ጠላት እንዲሆን አደረገ ዛሬም ወያኔ በህዝብ ከፍተኛ ተቀባይነት ያላቸውን ተቃዋሚዎች በስመ አሸባሪነት ስንቱን ወደ ወህኒ ላከ ስንቱንስ ገደለ ስንቱስ ተሰደደ ታዲያ ይህንን ዘረኛና አምባገነን የሆነ መንግስት እራሱ ላወጣው ህግ እንኳን የማይገዛ አውሬ መንግስት እስከ መቼ ነው አሜን ብሎ መኖር የሚቻለው?

በቃ ግዜው አሁን ነው ኢትዮጵያን የወያኔ ክፉ ሴራ አላማ ተጠቂ ሆና ከማየታችን በፊት አሁን እንነሳ ሁላችንም ነግ በኔ የሚለውን ማሰብ ይኖርብናል። እኔ ምን ቸገረኝ ምኔ ተነካ የሚለውን የሃሳብ ጐዶሎ ትተን በጋራ ካልተነሳን ዛሬ በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለው በደል ነገ ወደ እኛ መምጣቱ አይቀሬ ነው ይሕንን ሕዝባዊ መሠረት የሌለውን

የወያኔ ዘረኛ መንግስት ለመጣል ለወሳኝ ትግል ዛሬ በጋራ ለአንድነት እንነሳ፡፡ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ

# ማሞ ሌላ ፎቶው ሌላ

Zewdinesh Nigatu /Alsfeld/

ቅጥ ያለው የወያኔ አብዮታዊ ዴሞክራሲ መርህ መነሻውና መድረሻው በውል የማይታወቅ ግራ የተጋባ ርእዩተ አለም አንግቦ የኢትዮጵያን ህዝብ አፍኖ ረግጦ ከመግዛቱም ሌላ ለረሃብ፣ ለስደት ዳርጐታል፡፡ ይባስ ብሎ ጠንከር ያለ ተቃውሞና ትግል የሚያደርጉትን ህብረተሰቡ ጆሮውን የሰጣቸውን በሃገራችን ምርጫ ይሁንታውን ያረጋገጠላቸውን ወያኔ ለአገዛዙ ስጋት የሆኑበትን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለማዳከምና እድሜውን ለማራዘም በወያኔ በተሞላው ፓርላማ የሽብርተኝነት ህግ በሚል ሽፋን ህግ ሆኖ እንደጸድቅ ተደረገ፡፡

ልብ በሉ ወያኔን መቃወም ሽብርተኝነትን መደገፍ ሆነ ማለት ነው፡፡ በዚህም መሰረት ጠንካራ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን አመራሮችና ጋዜጠኞች ወጣቶችን ከየቤታቸው አፍኖ በማሰር በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር ለሰላምና ለዴሞክራሲ የሚታገሉ ዜጐችን በአሸባሪነት በመፈረጅ በእስራትና በግርፋት እየተሰቃዩ ሲሆን በውስጥ በራሱ በወያኔ ውስጥ ጠንካራ የፖለቲካ አስተሳሰብ ያላቸውም ለእሱ ያልተመቹትን ደግሞ ሙስኛ በሚል ተመሳሳይ እጣ ፈንታ የደረሳቸው በርካታ ናቸው፡፡

ወያኔ እድሜውን ለማራዘም የተለያዩ የሃይል አማራጮችን ለመውሰድ የተገደደው ሃገር መምራት ስለማይችል፣ የጠራ የፖለቲካ መስመር እየተከተለ ባለመሆኑ፣ የህዝብን የልብ ትርታ ማዳመጥ ባለመቻሉ፣ የህዝቡ ቁጣ እየከፋና እየሰፋ በመምጣቱ ወያኔን ያስጋው ስለሆነ ፍላጐቱን በሃይል በመጫን ከህዝቡ ተነጥሎ ብቻውን እየተጓዘ መሆኑን በግልጽ ያሳያል። ታዲያ እስከ መቼ የወያኔን የተሳሳተ ዲስኩር ሃገሪቱ በማደግ ላይ ነች የስኳር እጥረቱን ነጋዴ ፈጠረው፣ የዳቦ እጥረቱን ዳቦ መጋገሪያዎች ፈጠሩት በሚል በርካታ ዳቦ ቤቶች ታሽገዋል፡፡ ስንዴ በማከፋፈል እያረጋጋን ነው እነዚን እርስ በእርሳቸው የሚጋጩ ህዝቡ ችግር ውስጥ መሆኑን በግልጽ የሚያሳዩ የማደናገሪያ ፕሮፓጋንዳዎች እየሰማን ህዝቡ በኑሮ ውድነት እየተሰቃየ ዝም ብለን ልንመለከተው አይገባም በተባበረ ክንዳችን ከህዝባችን ጫንቃ ላይ ልናነሳው ይገባል፡፡

# ምን ማድረግ ይገባናል?

Samuel Taye Shebeshi /Amberg

ወያኔ ለም መሬት የመሸጥ ፉክክር ውስጥ በመግባት ለባእዳን ለም መሬትን በሄክታር በዝቅተኛ ዋጋ እየሸጠ ይገኛል፡፡ ቻይና ህንድና ሌሎች አገራት ደግሞ የመሬት ግዥውን እንዲያጧጡፍ የአገራቸውና ቱጃሮች እያበረታቱ ይገኛሉ፡፡ በብር መርከስ ምክንያት የሚፋፋ ንግድ ያለው የመሬት ሽያጭ ብቻ በመሆኑ የኢትዮጵያ ለም መሬት በሳንቲሞች በመቸርቸር ለባእዳን አስረክቦ የማንወጣው ማጥ ውስጥ ሊያስገባን አቅዶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡

በአሁኑ ጊዜ በሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ የምግብ እርዳታ ያስፈልገዋል ነገር ግን ብዙ ሄክታር ለም መሬት ለቻይና ፡ ለህንድና ለሳውዲ አረቢያ....! እየቸበቸበ ያለ ለዛውም የሚያመርቱትን ምርት ለአገራቸው ለሚልኩ ወያኔ ለራሱ ካልሆነ በስተቀር ለማንም ደንታ የለውም፡፡ ይህንን ከተረዳን ደግሞ ዘላቂ መፍትሄዎች ላይ ማተኮር ይኖርብናል፡፡ ስለዚህ የወያኔ መንግስት ከድርጊቱ እንዲታቀብ የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን አረመኔያዊ ድርጊት ለማስቆም በጋራ መንቀሳቀስ ይገባዋል፡፡

# ኢትዮጵያ መጨረሻዋ ምን ይሆን?

Alem Demeke /Gladenbach

የኢሕአዴግ መንግስት በአሁኑ ሰአት እያደረገ ያለው ቢጋምቤላ የሚኖሩ ሕዝቦች በተወለዱበት በኖሩበት አገር እንዲሰደዱ እያደረገ ቦታቸውን ለዛሮች ለወሬ አቀባዬች እየሸነሸነ እያከፋፈለ ይገኛል ድሃ ምንም የሌለው በየጫካው እየተሰደደ መድረሻ አጥተው በሥቃይ ላይ ይገኛሉ፡፡

በአሁኑ ሰአት ሕዝቡ በአቅሙ እንኳን ኑሮን መኖር እንዳይችል ይባስ ብሎ በምግብ ሸቀጦች ላይ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ አደርገ ሕዝቡ መድረሻ አጣ በጣም ተሰቃየ ለማን ነው አቤት የሚባለው ታፍኖ የቁም ሞት እየሞተ ይገኛል እባካችሁን የአለም መንግሥታት ለምን ይህንን የሕዝብ ስቃይ ችግር አትመለቱም እባካችሁን ኢትዮጵያን ነጻ አውጧት፡፡

# ውድቀት ለወያኔ

Fikirte Wolde /Tirschenreuth

ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ሙብቱ ተረግጦና ተደፍሮ በሀዘንና በችግር ሞትን ሳይፈራ ሀገሩን ለማስከበር ጦርና ጋሻን ሳይለይ እየታገለ ይገኛል፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ በሃገራችን ኢትዮጵያ እለት በእለት በሃዘንና ችግር እርሃብና ጥማት ስር እየሰደደ ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን ሁኔታ ለመለወጥ በምትኩ ሃገራዊ አንድነትንና ሉአላዊነትን ጠብቆ በነጻነት በዲሞክራሲና በእኩልነት ተፋቅሮና ተቻችሎ ለመኖር በዘረኝነት የተኮፈሰውን በስልጣኑ የተመከተውን የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ከዚህ በኋላ እንዳይቀጥል እኛም በውጭው ሃገር የምንኖርና በሃገር ውስጥም የምትኖሩ መለስ ዜናዊን ለፍርድ ለመቅረብ ቆርጠን እንነሳ፡፡

ሰላም ለኢትዮጵያ ሃገራችን ይሁን

# ፍርሃትን ማሸነፍ፤ ወያኔን ማስወገድ

Abey Ahmed Shemsu /Biedenkopf

በሕዝብ ውስጥ ፍርሃትን ማንገስ የተለመደ የአምባገነኖች መሳሪያ ነው፡፡ ፍርሃት ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ዜጐች ተዋርደው ተረግጠውና ተንቀጥቅጠው እንዲገዙ የማድረግ አቅም አለው፡፡ ፍርሃት ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ገገሮች የሌላቸውን ጉልበት ያላቸው ያስመስላል፡፡

ሆኖም ግን ፍርሃት ያቆመው ስርአት ለመናድ ጊዜ አይፈጅበትም ፍርሃት ያቆመው የበርሊንን ግንብ በሠአታት ውስጥ ፈራርሶአል። በፍርሃት ሕዝባቸውን አንቀጥቅጠው የገዙ የቱኒዚያ ቤኒ አሊ፣ የግብጹ ሙባረክ፣ እና የሊብያው ጋዳፊ ፍጻሜያቸው እንዴት እንደ ነበር ከጥቂት ወራት በፊት ያየነው ነው። ሕዝባቸውን በፍርሃት ቀፍድደው በመግዛት የታወቁት የየመኑ አብዳላህ ሳላህ እና የሶርያው ባሽር አልአሳድም ሊደረመሱ ተቃርበዋል። ኢትዮጵያዊያንን በፍርሃት ቀፍድዶ እየተጫወተበት ያለ የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ውድቀትም ተመሳሳይ እንደሚሆን ጥር ጥር የለንም። ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ

# የፖለቲካ ምህዳር በኢትዮጵያ

**Minewer Abdulwahid/Hof**

ኢ.ኤ.አ በ1991 ኢትዮጵያ በዘር ፌደራሊዝም ስትመሠረት ክልላዊ የሆኑ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሰፊው መታየት ጀምረው ነበር። ነገር ግን በ2005 ሁለት ሀገር አቀፋዊ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከተመሠረቱ በኋላ በዛው አመት በተደረገ ምርጫ ገዢው ፓርቲ ሙሉ በሙሉ መሸነፍን ተከትሎ በየጊዜው ነጻ የዲሞክራሲያዊ አስተሳሰቦችን የሚጻረሩ ህጐች መውጣት ጀመሩ። ከነዚህም መካከል የሚዲያ መተዳደሪያ ደንቦች፣ የሲቪክ ማህበራት ህጐችና የጸረ ሽብር ህጐች በዋናነት የሚጠቀሱ ሲሆን በህግ ሽፋን እነዚህ የወያኔ ህጐች አሁን እየታየ ላለው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር መጥበብ ያሳደሩትን ተጽእኖ እንመልከት።

የሚዲያ ህግ ተብሎ በወያኔ ፓርላማ የጸደቀው ህግ ጋዜጠኞችን ከሙያ ስነ ምግባራቸው ውጪ የሚያደርግ ሲሆን የሚዲያ ተቋማት ባለቤቶችንም በፍርሃት በማሸማቀቅ በስራቸው ላይ ጉልህ ተጽእኖ ከመፍጠሩም በላይ ዜጐች ሃሳባቸውን በነጻነት እንዳይገልፁ የሚገድብ ነው። ከዚህም ባሻገር ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የድርጅታቸውን ፕሮግራም በሰፊው ለማስተዋወቅ እድሉን ስለማያገኙ በሃገሪቱ የፖለቲካ ምህዳር መጥበብ ላይ የቀጥታ ተጽእኖ አሳድሯል።

በሌላ በኩል በሲቪክ ማህበራት ላይ የተደነገገው ህግ እነዚህ ማህበራትን የገንዘብ አቅማቸውን ለማዳከም 90 በሙቶ የሚሆነውን በጀታቸውን ከሃገር ውስጥ ማግኘት አለባቸው ከዛ ውጪ የሆነውን የፌደራል መንግስት ይቆጣጠረዋል ስለሚል አቅማቸውን ከመፈታተኑም በላይ በሃገሪቱ ውስጥ እየተከሰተ ባለው ሰብአዊ ሙብት ጥሰትና የጭቆና አገዛዝ ላይ አስተያየት እንዳይሰጡ ስለሚያስገድዳቸው የወያኔ መንግስት የሀገሪቱን የፖለቲካ ምህዳር በብቸኝነት እንዲቆጣጠር ከማስቻሉም በላይ በሀገሪቱ የአማራጭ አስተሳሰብ እድሎች ሙሉ በሙሉ እንዲጨልሙ አድርጓል።

ስለሆነም ለሀገራችንና ለህዝባችን ነጻነትና ነጻ የፖለቲካ አስተሳሰብ ስንል በሚቻለው መንገድ ሁሉ የወያኔ መንግስትን ከሥልጣን ማስወገድ ይኖርብናል።

# የሕዝባችን እጣ ፋንታ

**Dawit Mamo/Aschaffenburg**

ዘረኛው የወያኔ መንግስት ስልጣን በጉልበት ከተቆናጠጠ እነሆ ሁለት አስርት አመታትን አስቆጥረዋል። ይሁን እንጂ ሀገሪቷን በጐሣ በዘርና በሃይማኖት ከመከፋፈል በቀር ለኢትዮጵያ ሕዝብ የፈጠረ አንዳችም ፋይዳ የለም። የወያኔ የይስሙላ ባለሥልጣናት ሥለ ሃገራችን እድገት የውሸት ጥሩንባ ከመንፋት ያለፈ እውነታውን ስናይ ሃገሪቷ በአለም ላይ ከመጨረሻ ድሃ ከሚባሉ ሃገሮች ተርታ ትሠለፋለች። የሕዝቧ የኑሮ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁልቁል እየወረደ ነው። በተቃራኒው የጥቅም የዘረኛው መንግስት ባለሥልጣናትና ዘመዶቻቸው ኑሮ ከመጠን በላይ ሲጨምር የተንደለቃቀ ኑሮ ይኖራሉ። በሃገራችን ሁለት አይነት ሕዝብ ይኖራል ማለት ይቻላል። ይህ የአሠራርና የአመራል ብልሹነት ጥቂቶችን ሲከስ ብዘሃኑን ጉድቶታል።

የዘረኛውን መንግስት የአሠራርና የአመራር ብልሹነትን የሚቃወምና የሚተች ማንኛውም የሃገሪቷ ዜጋ ይታሠራል ይገደላል ይህ ደግሞ ምንም አይነት ፍትህና ዲሞክራሲ አለመኖሩን ያሣየናል። የድምጽ አልባ ማህበረሰቦች የወደፊት እጣ ፋንታ በአሁኑ ጊዜ በአሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል። ዛሬ እያንዳንዳችን የሕዝባችን እጣ ፈንታ ምንድነው ብለን የምንጠይቅበት ወቅት ላይ ነን። መልሱንም በጋራ መፈለግ የግድ ይለናል። ይህም በጋራ ተባብረን የጋራ ጠላታችን መጣልና ፍትህና ዲሞክራሲ ለሀገራችን ሕዝብ በማምጣት የህዝባችንን እጣ ፋንታ መወሰን ግድ ይለናል።ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ

# ፍትህ ያጣ ሕዝብ

**Priest Girma Abebe/Aschaffenburg**

ለማን አቤት ይባላል በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ትክክለኛ ፍትህ በማጣት እየደረሰ ያለ በደል፣ ግፍና ሰቆቃ እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል። በዘረኛው የወያኔ ፓርቲ መሪ በመለስ ዜናዊ መመራት ከጀመረ ወዲህ ፍትህና ዲሞክራሲ ተናፋቂ ሆነዋል።

ስለ ሙብቱና ፍትህ የሚናገር ካለ እስራት፣ ግርፋት፤ ዛቻና አፈና ይጠብቀዋል። ለገዥ ፓርቲ አደገኛ ነው ተብሎ ከታሰበ ደግሞ ያለ ምንም ጥያቄ ይገደላል። ይህ ደግሞ በአሁኑ ወቅት የሕዝባችን እጣ ፋንታ በአደገኛ ደረጃ ላይ መሆኑን ያሳያል። ስለ ፍትህ ዲሞክራሲ ማሰብ የማይቻልበት ዘመን ላይ ነን ማለት ይቻላል። ነጻ ፕሬስ የተከለከለበት አገር፣ ፖለቲከኞችና ጋዜጠኞች በግፍ የሚታሠሩበትና የሚሠቃዩበት አገር ውስጥ ስለ ነጻነትና ዲሞክራሲ ማሰብ ቅዥት ይመስለኛል።

ውሸትና ማስመሰል ባህሉ የሆነ ዘረኛው የወያኔ መንግስት እርዳታ ከምእራቡ ዓለም ለማግኘት በኢትዮጵያ ውስጥ መልካም አስተዳደር፣ ዲሞክራሲና ፍትህ አለ ብሎ ባዶ ፕሮፓጋንዳ ቢያደርግም ሃቁ ግን የተገላቢጦሽ ነው። ዛሬ ፍትህ የናፈቀው ሕዝብ በጋራ የሚያስተባብረው ቢያገኝና በተባበረ ክንድ ቢነሣ የወያኔ መግቢያ እንደሚጠፋ ጥርጥር የለኝም። ለዚህም ጊዜው አሁን ነው። ለጋራ ጉዳያችን በጋራ ተባብረን በእግዚአብሄር አጋዥነት እንታገል። የተባበረ ክንድ ያሸንፋል!

# ወያኔ በሴቶች ላይ የሚያደርሰው በደል ይበቃል

**Naomi Tesfaye /Höchstadt/**

ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ ሴቶች እጅግ በጣም ከባድ ሀላፊነት ተሸክመው ቆይተዋል በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው እውነታ በግልጽ የሚያሳየው ሴቶች አሁንም አሰቃቂ የሆነ ጭቆናና አፈና እየደረሰባቸው እንደሆነ ዛሬም መሰረታዊ የሆኑ መብቶቻቸውን ለማስከበር እየታገሉ መሆናቸውን ነው፡፡

ሴቶች እህቶቻችን ከፍትህ እጦትና ሰብአዊ መብት አለመከበር የተነሳ ወደ መካከለኛው ምስራቅ አረብ ሃገር በኮንትራት ስራተኝነት እየተላኩም ይህ ነው የማይባል የአካልና የአእምሮ ሰቆቃ ማለትም መደፈርን ኢ-ሰብአዊ የሆኑ በደሎችና መደብደብን የሚጨምር ግፍ እየተፈፀመባቸውና ለሞት እየተዳረጉ ነው፡፡

ሁሉም የኢትዮጵያ ዜጐች እንደተከተሉት ሴቶችም በነጻነት የመደራጀት እንዲሁም በሃገሪቱ የፖለቲካ የማህበራዊ ጉዳዬች የኢኮኖሚ ዘርፎች ዙሪያ ሀሳባቸውን በነጻነት መግለጽ እንዳይችሉ መብቶቻቸውን ተነፍገዋል፡፡ የገዥው ወያኔ ቡድን ሃሳብን በነጻነት መግለጽ እንዳይቻል በሚያደርገው አፈና ምክንዮቶች ሴቶችን በማፈን በስቃይ እንዲኖሩ አስገድዷቸዋል፡፡ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ለፍትህና ለፖለቲካ መብቶች የሚታገሉ ሴቶች ይዋረዳሉ በአሰቃቂ ሁኔታም ይታፈናሉ፡፡

ምንም እንኳን በገዥው ፓርቲ አማካኝነት ተወዳዳሪ የሌለውና በስልት የሚካሄደው አፈና ቢኖርም ታሪክ በተደጋጋሚ የመሰከረው ነገር ቢኖር አፈና ለዘለአለም ሊቀጥል እንደማይችል ነው፡፡ እኛ ሴቶች ይህንን ግፍና በደል ለመታገል ከወንድሞቻችን ጐን በመቆም ልንታገለው ይገባል፡፡

# በህብረት እንነሳ

**Senaiye Kifle Kibebe /Höchstadt/**

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ መንግስት የኢትዮጵያን ሕዝብ በግፍ መግዛቱን ሊያቆም የሚችለው በህብረት መቃወም ስንችል ነው፡፡ ወያኔን ከስልጣን ላይ ማውረድ ከቻልን ስደት ጭቆና ዘረኝነትና አድሎ ይወገዳሉ በምትኩ በሃገራችን ሃብት መጠቀም እንችላለን የሃገር እድገት የሚኖረው ዘረኝነትና መከፋፈል ሲቆም ብቻ ነው ለስደታችን ትልቁ ምክንያት የሆነው የወያኔ በጭቆና የተሞላ የግፍ ስርአት ነው፡፡

ከዚህ አስከፊ የጭቆና አገዛዝ ለመላቀቅ በየዘመናቱ ዜጐች የፍትህ ጥያቄ ማንሳታቸው አልቀረም ነገር ግን ጥያቄዎቻቸው በወንጀለኛነት እየተፈረጁ እነሱም የአምባገነኑ የጥቃት ሰለባ ሲሆኑ ኖረዋል ይኖራሉም። አምባገነኖች ግን የአፈና መረባቸውን ዘርግተው በማንአለብኝነት ሃገርን እያጠፉ ታሪክ ይቅር የማይለው ወንጀል በዜጐች ላይ ያለ ርህራሄ እየፈጸሙ የሃገር ሃብት እየመዘበሩና እያስመዘበሩ የተሻለ ስርአት በመገንባት ላይ እንገኛለን ይሉናል፡፡ እንዲህ አይነቱን ሸፍጥ የፖለቲካ ውንብድና ካልሆነ በስተቀር ከቶ ምን ሊባል ይችላል?

ስለዚህ የወያኔን አገዛዝ የምንጥለው በህብረት ሆነን ስንታገል ነው፡፡ ስለዚህ በፍቅር ስንተሳሰርና በአንድነት ስንተባበር የወያኔን አምባገነን መንግስት ለመጣል በህብረት እንነሳ፡፡ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ

# ነጻነትና ነጻ መውጣት ለኦሮሞ ሕዝብ

**Fesseha Tefera /Höchstadt/**

በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ አምባገነን መንግስት በኦሮሞ ህዝብ ላይ እያደረሰ ያለው ግፍና በደል ህዝቡን ለባርነትና ለስደት ዳርጐታል፡፡

የወያኔ መንግስት በሚያደርስበት ከፍተኛ ኢ-ሰብአዊ ተጽእኖ አሁንም የኦሮሞ ተወላጆች ነጻ ሊወጡ አልቻሉም የመናገር መብታቸውን የሚያስከብሩበት ነጻ መድረክ ባለማግኘት እስከ ዛሬ ድረስ በበታችነት እየተረገጡ ይገኛሉ፡፡

በአሁኑ ሰአት አምባገነኑ የወያኔ መንግስት በኦሮሞ ህዝብ ላይ እያደሰ ያለው ግፍና በደል ስቃይ ምንም አይነት ለውጥ ያልተገኘለት ጉዳይ ነው፡፡ እንደውም የዚህ መንግስት በኦሮሞ ህዝቦች ላይ እያደረሰ ያለው አፈና ግድያና እስር ከምንጊዜውም በላይ እየጨመረ የመጣበት ጊዜ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ሆነም ከኢትዮጵያ ውጭ ለኦሮሞ ህዝብ አምባገነኑን የወያኔ መንግስት ስቃይና ጭቆናና አፈና ግድያ ርሃብና እርዛት እስራትና ስደት የሚያበቃብትና በህብረት ሆነን የምንታገልበት ጊዜው አሁን ነው፡፡

የዚህ ጨቋኝና አረመኔያዊ አገዛዝ አክትሞና አብቅቶ በምትኩ ለውጥ የምናመጣበት የኦሮሞ ህዝብ በሃገሩና በንብረት በመሬቱ መኖር የሚችልበትን ጊዜ ሁላችንም በጋራና በህብረት ሆነን ለውጡን እናፍጥን፡፡ እናም በአለም ላይ ያሉ የሰዎች መብት ታጋዮች የኦሮሞን ህዝብ ጉዳይ በትኩረት እንዲመለከቱት ሠፊው የኦሮሞ ሕዝብ ይጠይቃል፡፡

# ባገሩ የሌለ የትም የለም

**Mera Abraham Abebe /Höchstadt/**

ሃገራችን ኢትዮጵያ የዘሩባትን የምታበቅል ለምለም ማህጸን ናት፡፡ ከማህፀኗ የወጡት ልጆቿም ሃይማኖት ዘርና ጐሳ ሳይለያቸው በአንድ ገበታ ላይ ተቀምጠው ሃገራችንን ዳሯን እሳት መሃሏን ገነት ያድርግልን ተባብለውና ተመራርቀው በፍቅርና በመተሳሰብ ለበርካታ ሺህ ዓመታት ኖረዋል፡፡ የሀገርን ክብርና ልእልና ጠንቅቀው ስለማያውቁ እንዳለመታደል ሆኖ ሃገራችን አስተዋይ፣ አገሩንና ህዝቡን የሚያሸብር መሪ ግን አልታደለችም፡፡ በተለይም ላለፉት አምስት አሰርት ዓመታት በዚህም ምክንያት አሁን ድረስ አገሪቱ እጆቿን ለልመና ህዝቦቿም ለችግርና ለስደት ተዳርገናል፡፡

በስልጣን ላይ ያለው አምባገነኑ የወያኔ ስርዓት ዛሬም ንፁሃን እህቶቻችንና ወንድሞቻችንን ያስራል፣ ይደበድባል ፣

ይገድላል፡፡ የኑሮ ውድነቱም ወደ ላይ ሲወጣ እንጂ ሲወርድ አይታይም፡፡ በዚህም ምክንያት በብዙ ወገኖቻችን ጓዳ ውስጥ የሚላስ የሚቀመስ እየጠፋ ለሞትና ለስደት እየተዳረገ ነው፡፡ እኛም ዛሬ በስደት ላይ ያለነው ኢትዮጵያዊያን ያለፈው ጊዜ የቱንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆንም እንደገና መጀመር ይቻላልና ለሃገራችንና ለወገኖቻችን ያለንን ፍቅርና አክብሮት በአንድነት በመቆም የወያኔን ስርዓት ለመጣል በተግባር መንቀሳቀስ ይጠበቅብናል፡፡

የስደት በቃ የለውም ብለዋል ታላቁ ገጣሚና ደራሲ ፀጋዬ ገ/መድህን ሁሉም ስደተኛ ተመሳሳይና አንድ ዓይነት ህይወት መጋፈጡን ሲያሳዩን በተለይም ባገር የመኖርን እንቁነት ሲያዳሉት፡፡እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ አሜን

## የወያኔ የግፍ አገዛዝ ይብቃ

**Dawit Lemma /Regensburg**

ወያኔ ሕዝባችንን ነፃነት በማሳጣት ወግና ባሕሉን እንዲሁም አንድነቱን ጠብቆ የኖረውን ውድ ኢትዮጵያዊ ወገን በዘር በሃይማኖት በመከፋፈል አንድነቱን አሳጥቶታል፡፡

እንዲሁም በተጨማሪ በዲሞክራሲ ስም እጅግ ብዙ የማጭበርበሪያ ስልቶችን እነሆ በሰፊው በማራመድ ላይ ይገኛል፡፡ እንዲሁም በተጨማሪ ወገንን ሰላምና አማራጭ በማሳጣት ለስደትና ለመከራ /ለመንገላታት/ ዳርጐታል፡፡ ይህ እስከ መቼ በዚህ ሁኔታ እንደሚቀጥል ባይታወቅም ይህንና የመሳሰሉትን ፀረ ዲሞክራሲና ፀረ ሰብአዊ መብት የወያኔ እንቅስቃሴ እንዲገታ ኢትዮጵያዊ የሆነ ወገን ሁሉ በአንድነት በመተባበር ወያኔና ለማስወገድ ትግል ማድረግ ይገባዋል!!

## በአንፃራዊነት

**Dawit Muse/Münnerstadt**

ኢትዮጵያ በረጅም ዘመናት ታሪኳ ከአራቱም ማእዘናት ለወረራ የመጡባትን የውጭ ተስፋፊ ሃይሎች ጋር መታገሏ የሚዘከር ሲሆን እኛን ሕዝቦችዋ የሚያስደምመን ከታላቋ ሮማ ፋሽስት መሪ መሶሎኒ ሌሎችም ታላቅ ነን ብለው ትጥቃቸውን ሰራዊታቸውን የቴክኖሎጅ አቅማቸውን አደራጅተው ኢትዮጵያን ደበደቡ ቅርሶቻችንን እሴቶቻችንን አወደሙ እንጂ አባቶቻችንን አላሸነፍም አሸንፈውም አያውቁም። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያን በአንፃራዊ የታሪክ ሙሕራኖች እንደሚገልፁት ጥንት ታስተዳድራቸው የነበሩ ግዛቶች ሰፊ መሆናቸውን ይዘግባሉ፡፡ ነገር ግን ከሩቅ ከመጡት ታላቅ ነን ባይ ወራሪዎች ባሻገር የሶማሊያው መሪ ሀገራችንን ሲወር ታላቋ ሶማሊያን ብሎ እንደተነሣ ሁሉ ወያኔ ያስገነጠላት ኤርትራም የምስራቅ አፍሪካ እስራኤሎች ነን ብለው በታላቅ ሃገር ላይ ጦርነት ሲያውጅ የሚገርመው የሩቅ ተስፋፊዎች ባላደራ መመሣሠላቸው ነው፡፡ ታላቁ መጽሃፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ንጉስ ዳዊት ጠላቶቹ በተነሱበት ጊዜ ከቤተልሄም ውሃ ሊጠጣ ወደደ ጭፍሮቹም ተዋግተው ሊጠጣ የወደደውን ውሃ አመጡለት ንጉስ ዳዊት ሕይወታቸውን ስለሱ ከፍለው ደማቸውን አፍሰው እንዳመጡለት ባየ ጊዜ ሊጠጣ የወደደውን ውሃ አፈሠሠ ናቀ ይለናል፡፡ ሆኖም በዚህ ክፍለ ዘመን ዘግናኝ የተባለለት በሙቶ ሺ የሚቆጠር ወጣት የረገፈበት ጦርነት እውነት ለኢትዮጵያ ጥቅምና ፍላጐት ሆኖ ቢሆን ጠቅላይ ሚኒስትራችን ከምጽዋና አሰብ ሊጠጡ እንደወደዱት ውሃ ሠራዊቱ አጥንቱና ደሙን ከከፈለበት ይዞታ ለቀህ ውጣ ባላለ ነበር፡፡

ኢትዮጵያዊው ጀግና የውጊያ አበጋዝ ድንበሬ ቀይ ባህር ነው ፈረሴን ውሃ ሣላጠጣ ስበበበ

አልመለስም ሲል አሉላ አባነጋ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአንፃራዊነት እንደወርቅ በእሳት ከተፈተነው የትግራይ ሕዝብ በመወለዴ እኮራለሁ ነበር ያሉን።አለም አንድ መንደር ሆናለች በሚባልበት ዘመን ወያኔዎች መቼ ይሆን በዘር ከመከፋፈል መርዘኛነት የሚላቀቁት መቼ ይሆን ኢትዮጵያን እንዲወሠድባት ከመስራት እንዲሠጣት የሚሠሩበት መቼ ይሆን የይግባኝ አደባባይ የሚቆሙበት እንግዲህ ኢትዮጵያዊነት ትርጉሙ ከጠፋበት አፋኝ የወያኔ አመራር ወጣቱ ትውልድ ምንም ሊጠብቅ አይገባውም ነፃነትና ዲሞክራሲ በትግልና በመስዋትነት የሚገኝ እንጂ በስጦታ የምንቀበለው እንዳልሆነ ተረድተን ከኔ ከአንቺ መቼ እና እንዴት ምን ይጠበቅብናል? ልንመልሰው የሚገባ ወቅታዊ ጥያቄ ነው፡፡ ምክንያቱም ታስረናል፣ ተገርፈናል፣ ተገድለናል የተረፍነው ተሠደናል፡፡ የቀረን አንዳች የለንምና ዛሬ ወስን ዛሬ ወስኝ!!!

## ለስደት የዳረገን የወያኔን መንግስት በአንድነት እናስወግደው

**Biruk Hailu /Regensburg**

ለስደት የዳረገንን ጨቋኙን የወያኔን ሃይል ህዝባችን በተወለደበት ባደገበት አገር እንደ ባይተዋር ነፃነቱን አጥቶ በሀገር እንዳይኖር ጭቆናን ጠልቶ ሃገሩን ወገኑን ትቶ በስደት ላይ ነፃነትን ፍለጋ እየተሰደደ ያለውን ወገናችንን ልንታደገው የምንችለው በኋላ ነፃነታችንን የምናገኝበት መንገድ ሊገኝ የሚችለው አሸባሪው የወያኔ መንግስት በአንድነት ሆነን መታገል ስንችል ብቻ ነው ነፃነት የጠማውን ተጨቁኖ ያለውን ሕዝባችንን በስደት ላይ ያለን ወገኖች በሞላ ወያኔ ከስልጣኑ የሚነሳበትን መንገድ እንፈልግ፡፡

## ነጻ ምርጫ ናፈቀኝ

**Fitsum Ayalsew /Regensburg**

ኢሕአዴግ የሚገርም መንግስት ሆኗል፡፡ ኢሕአዴግ ከጥቂት አመታት በፊት ነጻ ምርጫ አደርጋለው ብሎ ነበር በሚገርም ሁኔታ ሸንፈትን የተከናነበው ከዛሬ በፊት ይኸው መንግስት ጠንካራ ተቃዋሚ ለማግኘት አልታደልኩም

እንዳላለ ሲሸነፍ ደሞ በጭራሽ አልተሸነፍኩም ብሎ የልጅ ጨዋታ ጀመረ።ኮሮጆ ተሰረቀ እያለ የምርጫ ሳጥን አዘጋጅቶ እየቀየረ እራሱ አመጽን እየፈጠረና በዛው ሰበብ የሚፈልጋቸውን ሰዎች እያሰረ በተጭበረበረ ምርጫ ስልጣኑን ይዟል። ስለዚህ የኢሕአዴግን የውሸት ምርጫ ተረድተን ድምፃችንን ከፍ አርገን ተቃውሞአችንን ልናሰማ ይገባል፡፡

# የወያኔ አገዛዝ ይብቃን

Meseret Mengesha /Regensburg

ነፃነት ለአንድ ሃገር ኢኮኖሚ የፖለቲካ እድገት ጠቃሚና ትልቅ አስተዋጾ አለው። አምባገነኑ የወያኔ ስርዓት የግፍ አገዛዙን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በመጫን መሪርና አስከፊ ተግባራትን በመፈፀም ሕዝቡን በማመስ ላይ ያለ ፀረ- እድገትና ፀረ- ሰላም ሆኗል። ታዲያ ኢህን ስርዓት በጋራ በመሆን መዋጋት አለብን። ለአንድ ሃገር እድገት መልካም መሪና አመራር ትልቅ አስተዋጾ አለው ስለዚህ የሰላም ብርሃናችንን ለመጐናፀፍ አንባገነኑን መሪ ከስልጣን ማውረድ አለብን፡፡

# በኦሮሞ ሕዝብ ላይ በደል የሚያደርሰው የመለስ አገዛዝ ይብቃን!/

Melaku Tesfaye/ Höchstadt/

በኦሮሞ ነፃነት ግንባር አንድነት ከፍተኛ ስጋት ውስጥ የሚወድቀው የወያኔ ስርዓት ዘንድሮ ጉድ የፈላበት ይመስላል። ይህን ሰፊ የሆነ አንድ ሕዝብ አንዲት የጋራ ሐገር አንድ የጋራ እድል ያለው በመሆኑ ከጎሰኛ አገዛዙ ወያኔ በላይ የሚያሳስበው የለም።ከዚህም በመነሳት የዚህን ሕዝብ አንድነት ለመሸርሸር ያልቆፈረው ጉድጓድ ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም።አልሆነለትም አልተሳካለትም እንጂ!

ዋናው የኦሮሞ ሕዝብ አቅምና ጥንካሬ አንድነቱ በመሆኑ ይህን አንድነት በመሸርሸር ሕዝቡን ለዘላለም ከጭቆና ቀንበር እንዳይላቀቅ ማድረግ ምንግዜም ቢሆን የኦሮሞ ሕዝብ ጠላቶች ሕልም ነው።የህልም እንጀራ ሆኖ ቀረ እንጂ።

ወያኔ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ የሚያደርሰው በደል በዚህ ብቻ አያበቃም።ይባስ ብሎ ህዝቡን በረሀብ እየቀጣው ይገኛል። አሁን አሁንማ እንደውም ስለ ኦሮሞ ሕዝብ መብት የሚጠይቅ ሰው የእስርና የግርፋት ሲገፋም እስከ ሞት የሚያደርስ ቀጣት እየተከናነበ ነው።ምንም እንኳን የህዝቡን የተቀጣጠለ ትግል ባያበርደውም።

ወያኔ ሐገር ሲያፈርስና ሲንድ ሕዝብን በጎሳና በስፍራ ሲያጋጭና ሲያበጣብጥ ለም መሬት ለባእዳን ሲሸጥ ሐገሪቱን ወደብ አልባ አድርጎ ባዶ እጅ ሲያስቀር በ21ዓመታት ስልጣን ቆይታው በሰው ልጆች ላይ ከፍተኛ በደል አድርሷል። አረመኔው የወያኔ ቡድን በኦሮሞ ሕዝብ ላይ የሚፈፅመውን እስርና ግፍ እንቃወማለን! ያለ ሰብአዊ መብት ያለ ዲሞክራሲ ያለነፃነት ልማት የለም። ያለ እኩልነት ልማት የለም ሰለሆነም ገበሬዎችን ከመሬታቸው ማፈናቀሉን አጥብቀን እንቃወማለን። መሬት ለባእዳን መቸብቸቡን እንቃወማለን! የታሰሩት የፖለቲካ እስረኞች በህይወት መኖራቸውን እርግጠኛ መሆን አልቻልንም።የአምባገነኑ አገዛዝ ይብቃ! No investment without democracy! No investment without freedom! ፀረ ወያኔ ህዝባዊ ትግላችን ይፋፋም!!!ድል ለኢትዩጵያ ሕዝብ

# ዘረኝነትን ማዕከል ያደረገው የወያኔ አገዛዝ

Rahel Efrem /Forchheim

መሰረቱ ህብረ ብሄር የሆነ እንደ ኢትዩጲያ ያለ ሕዝብ ከዝቅተኛ እድገት እርከን ወደ ላቀ ደረጃ ለመሸጋገር ፅኑ መሰረት ላይ የቆመ ቀልጣፋ ማህበራዊ አደረጃጀት፤አሳታፊ የፖለቲካ ስርአት እና ተጨባጭ ውጤት ላይ ያተኮረ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ያስፈልገዋል። ሁሉም አይነት የፖለቲካ ወይም የኢኮኖሚ ፖሊሲ የራሱ ድክመት እና ጠንካራ ጎን እንዳለው ግልፅ ነው።

ይሁን እንጂ ሕብረተሰቡ ለእድገት ያለው ፍላጎትና ሰብአዊ ክብሩ በሕግ ተረጋግጦ የመኖር ትርጉም ፋይዳ የሚኖረው ተስፋ የሚያልምበት ብቻ ሳይሆን ተስፋውን በእውን ማየት የሚችልበት ሁኔታ ከመመቻቸቱ ላይ ነው።

የኢትዩጲያ ሕዝብ ስለ እድገት ስለ ፍትህ ስለ ሰላም እና ስለ እድገት ብዙ አልሟል ብዙ ተመኝቷል።የተመኘውንም ለመጨበጥ እጅግ ደክሟል።ብዙ መስዋትነትም ከፍሏል ትግሉም ሆነ መስዋትነቱ ዛሬም ቀጥሏል።

ወያኔ በሀገር አንድነትና ህልውና ላይ የደቀነው አደጋ እንዲወገድ በፅኑ የሀገር ፍቅር ስሜት ተሰልፈው የነበሩና ደማቸውን ውድ ሕይወታቸውን ቤዛ ያደረጉ ሰሜን ተራሮች ላይ የወደቁ ደማቸውን ከቀይ ባህር የቀላቀሉ ውድ ኢትዩጵያውያን ቤት ይቁጠራቸው።

በእርግጥ ነው ነፃነታችን እና አንድነታችን ተናግቷል።የኢትዩጲያ ሕዝብ ዛሬም ከምንጊዜውም የባሰ ተስፋው መከኖ አፈና በተንሰራፋበት ስጋት በሰፈነበት ሕይወት ውስጥ እያዘገመ ነው።በታሪክ አጋጥሞት በማያውቅ ደረጃ ረሀብ በሽታ እና ስደት እያንገላታው ነው።

ብሔራዊ ክብሩን በደም ያቀለመው ሕዝብ የጎጠኛ መዘባበቻ ሆኗል።ጎጠኝነትን ምርኩዝ አድርጎ የተነሳው ወያኔ ኢህአዴግ በሀገሪቱ ውስጥ የሚነሱ ፖለቲካዊም ሆነ ማህበራዊ ጥያቄዎችን የሚመዝነው በጎጥ መስፈርት ነው።ካርታ ቢስል ታሪክ ቢያወራ የፖለቲካ ሹመት ቢሰጥ ምርጫ ብሎ ቢሰለፍ ከትንሹ የንግድ ፈቃድ እስከ ግዙፉ ኢኮኖሚ አውታር ቁጥጥር የሚመለከት...ወዘተ ሁሉም ነገር በጎጥ መነፅር ተመዝኖ የጎጥ ክፍፍል የሚጠናከርበትን መሰረት ለማፅናት የሚከናወን ነው።

ወያኔ በስልጣን ላይ ከመጣበት ዘመን አንስቶ እየተገበረ ያለውን ጉዳዩች ማየቱ ብቻ ለዚህ በቂ ማስረጃ ይመስለኛል።ኑሮውን ለማሸነፍ እና ለማሻሻል የሚታገለው ሕዝብ የድካሙ ውጤት ተጠቃሚ የሚሆነው በራሱ ሙሉ ፈቃድ ሳይሆን ስልጣን ላይ በተቀመጠው ስርዓት ይሁንታ ብቻ ነው ።በዘር ግንድ

ላይ የተመሰረተ ስልጣን ብሔራዊ ራዕይ ሊኖረው አይችልም።የመላው ዜጋ አመኔታ ሊያተርፍ የሚችልበትን መንገድ አይገነባምና። ስለሆነም ወያኔ ባለፉት 21 ዓመታት ተደጋጋሚ ፈተና ተሰጥቶት መመለስ ተስኖት በመንገዳገድ ላይ በመሆኑ በተባበረ ክንድ ከመንበረ ስልጣኑ ልናስወግደው የሚገባን ጊዜ አሁን ነው!ድል ለህዝባዊ ትግላችን!!!

# በፍጥነት መወገድ ያለበት የወያኔ አገዛዝ

**Meriam Kuraw /widsbach**

ዘረኛውና አንባገነኑ የመለስ ዜናዊ አመራር የተቃዋሚ ዜጐችን ድምጽ ለማፈን ከፍተኛ ተጋድሎ እያደረገ ነው፡፡ ይሕን ሰብአዊ መብት ረገጣ ሁሉም ዜጋ በንቃት በአንድነት በመነሣት ሊያስቀረውና በበደልና በአሰቃቂ ግዛት የሚገኘውን ህብረተሰባችንን በአንድነት ሆኖ ሊታደገው፤ የወያኔን መራር አገዛዝ ሁሉም አገር ወዳድ ይበቃሃል በማለት ስርአቱን ለማስወገድ በአንድ ላይ ሆነን እንድንታገለው ጥሪዬን አቀርባለሁ።

# አሁንስ ይበቃል

**Daniel Zeleke /Hilpoltstein**

ዛሬ በአገራችን ያለው የተወሳሰበ ሁለገብ ችግር አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰው ህዝባችን በመንግስት አመሰራረትና በድርጅቱ እንቅስቃሴ ወሳኝነት ያለው ሚና መጫወት አለመቻሉ ነው፡፡ ከችግሮቻችን ሁሉ መሰረታዊ የሆነው ችግርም ከፖለቲካ ጉዳይ ጋር የተሳሰረ ችግር ሆኗል፡፡

በሀገራችን እንደዜጋ የማንቆጠር ህዝቦች ሆነናል። ህዝብ ሃሳቡን መግለጽ ያልቻለበት፤ዴሞክራሲ የሌለበት ነጻ ፕሬስ እንዳንጽፍ እንዳናነብ በአዋጅ ጭምር የታገድንበት ወቅት ነው። ይህን በመረዳትም ህዝቡ የወያኔን ስርአት ነቅቶ እየተዋጋ ነው፡፡በአንፃሩ ወያኔ ህዝቡን በረሃብ እና በችግር በማሰቃየት ሌት ተቀን እየሰራ ይገኛል፡፡

ወያኔ የራሱ ፓርቲ አባል ያልሆነውን ከሰው አይቆጥርም የወያኔ ፓርቲ ከውጭ ለሚያዩት ነጻ ዴሞክራሲያዊ ይመስላል፡፡ ነገር ግን ውስጡን ያየ በትክክል መረጃውን ያገኛል። ወያኔ በህገ-ወጥ መንገድ ምርጫውን አሸንፌአለሁ ሲል ማንም ሊከለክለው አልቻለም ለህዝቡ ጩኸት መልስ ስለሌለውም በጥይት ጭምር እየገደለ በአምባገነንነት ስልጣኑን ተቆጣጥሮ አገሪቱን እያመሰ ይገኛል፡፡

በሀገር ውስጥ የተፈጠረው በአድሎና በዘረኝነት ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ኢኮኖሚያዊ መዋቅርም በርካታ ዜጐች በሃገራቸው ባይተዋር እንዲሆኑ በማድረጉ ምርጫቸው እውቀታቸውን እና ጥሪታቸውን እየቋጠሩ መሰደድ ሆኗል፡፡ወያኔ ነጻነትን የማያውቅ መንግስት ነው። የወያኔ ስልጣን የተጨቆነውን የኢትዮጵያ ህዝብ ነጻ ላውጣ ያለ አይደለም፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ ይህንን ዴሞክራሲ የማይገባው አምባገነኑን ስርዓት ለመጣል ተግተን መነሳት አለብን፡፡ ነጻ እና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እንመስርት፡፡ ''ድል ለሰፊው ሕዝብ''

# በጋራ ከሠራን በወያኔ ላይ ተጽእኖ ማምጣት እንችላለን

**Zed Bekele /Hilpoltstein**

አምባገነኑ የኢትዮጵያ መንግስት የኢትዮጵያን ሕዝብን እንደ አሻንጉሊት በመቁጠር መጫወቱን እንደቀጠለ ነው። አሁንም አገሪቱን በአምባገነንነት የሚያስተዳድረው የወያኔ /ኢሕአዴግ/ መንግስት የሀገሪቱን ወጣቶች ሴቶችና አዛውንቶች ለመብታቸው ለነጻነታቸው ድምጻቸውን የሚያሰሙትን ሁሉ በማሳደድ በማሰር አልፎም ክቡሩን የሰው ልጅ አሳቃቂ በሆኑ እስር ቤቶች በማጐር ላይ ይገኛል፡፡

በተለያዩ የሀገሪቱ ግዛቶች የሚነሱ የደሞክራሲያዊ ጥያቄዎች ለማፈን የሚደረገው አፈና ተጧጡፏል መቼ ነው ይህ ሰቆቃ የሚያከትመው? ስለዚህ እኛ በውጭ ሃገር የምንኖር ኢትዮጵያዊያን በጋራ ከሠራን በወያኔ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ማምጣት እንችላለን ስለዚህ ዛሬ ሁላችንም በጋራ የጋራ ጠላታችን ወያኔን ለማስወገድ ከአርበኞች ግንባር ጐን እንቁም እያልኩ ጽሁፌን በዚህ አበቃሁ ።ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

# አሳፋሪው የወያኔ ድርጊት

**Bineyam Anteneh Seyaum / Tirschenreuth**

ኢትዮጵያዊያን የስደትና የመከራ የስቃይ ሕይወት በባእድ ሃገር እየገፉ ይገኛሉ፡፡ ስንቱ ምሁር ስንቱ ወጣት አገሩን በተለይ ሳይማር ያስተማረውን ወገኔን ለመርዳት ለማገልገል ያልቻለበት ወቅት ላይ ይገኛል። ይሕም ወያኔ ኢትዮጵያ ሃገራችንን ለምእራብና ለሃያላን መንግስታት ዴሞክራሲ የሰፈነባት የሰብአዊ መብት የተከበረባት ሆና ለድፍን አፍሪካ ተምሳሌታዊ ሃገር ያስመሰለበት የግፍ የጨለማ አገዛዝ የነገሰባት በ21ኛው ክፍለ ዘመን የለየለት ኋላ ቀር አገዛዝ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ሃገራችን በዘር፣ በሃይማኖት በቋንቋ በክልል ከፋፍሎ አንድነታችንን ለመፋቅ አትንኩኝ ባይነታችንን በማጥፋት የራሱን ቦታ ለሆዳቸውና ለግል ጥቅማቸው በሚያድሩ ካድሬዎች እውቀትና ችሎታ የሌላቸውን በማቀፍ ራሱ ባቋቋመው የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ አቅምና ችሎታ ባላገናዘበ የራሱን ፖለቲካ ስለራመዱ ብቻ የእውቅና ሰርተፍኬት ማስትሬት ዲግሪ በማሳቀፍ የሃፋረት ስራ እንደሚሰራ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያውቀው ሃቅ ነው፡፡

መለስ ዜናዊ እስከ ግብር አበሮቹ ለፍርድ ይቅረቡ !የሰው ልጅ መብቱ ምን ላየ እንደሆን እንኳን ሊያውቅ አልቻለም፡፡ መብት አለን ብለን ስንናገር ለእስራት ለግርፋት እንዳረጋለን ሌላው ደግሞ ስንቱ

ነው ድንበር ሲያቋርጥ የት እንደገባ እንኳን ሳይታወቅ የውሃ ሽታ ሆኖ የቀረው ይሕ ሁሉ የወያኔ ስራ ነው፡፡ሰላም ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

# ጉዞአቸው ወዴት ይሆን?

**Betewedaj Adnew /Bayreuth**

ውድ አንባቢያን ወገኖቼ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ጀርመናውያን ሰላምናችሁ አሜን ሠላም ይብዛላችሁ። ዋናው ነገር ሠላም ነው እኛም ሠላም አጥተን ከተወለድንበት ቀየ ስደትን መርጠን ሰላምን ሽተን የተሰደድነው።

እስኪ እናንተዬ ወደ ርእሴ ልግባላችሁ ሰላም ያሣጡን የእነዚህን የሀገራችን ጉዶች ነገር እንዲያው ልንገራችሁ ጉዞአቸው ወዴት ይሆን? የእነዚህ ሰላምን የማያውቁት ተሸሎክሏኪ መልክ አልባ እስስቶች ህዝቡን መቆሚያ መቀመጫ አሣጥተው ውጫዊ ቆዳቸውን አለስልሰው ውስጣቸው ግን እንደጦር እየተዋጋ ለእቤት ቀጋ ለውጭ አልጋ ሆነው የተለያዩ መንግስታትን በማደናገር እንደ ማራቶን ሩጫ እየገፋበት ሄደዋል አሁን ግን ይበቃል ልንላቸው ይገባል፡፡

ወገኖቼ ሆይ እስኪ እነዚህን ወያኔ /ሠይጣኔ/ የምንላቸውን ከሰሙን አንድ ጥያቄ ልጠይቃቸው። ሠላም ማለት ምን ማለት ነው በእነሱ አስተሣሠብ ሣይሆን በአለም ህዝብና መንግስት ሃሣብ ያለውን ያውቁት ይሆን? ይመስለኛል እነርሱ ሠላም የሚመስላቸው ጫካ እያለ እንደተማሩት እነሱ ብቻ ተደላድለው መኖር ሌላው ወገን መበደል መጨቆን ማሠር ማሠቃየት መግደል ከሆነ ተሳስተዋል።ስለዚህ ይሄንን ነገር አቁማችሁ ጉዞአችሁ የተጣመመ ነው እና አስተካክሉት መስተካከል ይገባዋል ጉዞአችሁ ወዴት እንደሆነ አታውቁም እና የሚያውቁትን ማማከር ሞት አይደለም ጠይቁ ተማሩ ሰላምን ሰላም ለናፈቀው ትውልድ አትንፈጉት አመሰግናለሁ፡፡

# ይህ ነው ዴሞክራሲ?

**Nesanet Alemayhu /Tirschenreuth**

ቃላቸው የት? ስራቸው የት? መጀመሪያ ኢትዮጵያን ሲገዙ ለመብት እንታገላለን፣ በደልና ጭቆናን እናጠፋለን ኢትዮጵያን ወደ ዲሞክራሲያዊ ስርአት እንለውጣለን ነበር፡፡

ታዲያ ዛሬ ለመብታችን እንታገላለን በሚሉት ብሄር/ብሄረሰቦች ላይ ያለፉት ስርአቶች ያደርሱ የነበረውን በደልና ጭቆና በእጥፍ ውስጥ ለውስጥ እያደረጉ ባሉት ስራ ሕዝባችንን ለርሃብ፣ ለእስራት፣ ለሞትና ለስደት እያበቁት ይገኛሉ፡፡ ኢትዮጵያን ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ማሸጋገር ያስፈልጋል የሚለውን እምነት የያዙ መሆናቸውን ሲናገሩ ምስኪኑ ያገሬ ሕዝብ አመናቸውና ሊቀበላቸው ሆ ብሎ ወጣ ታዲያ ከዛ በግልባጩ ሕዝባችን ዲሞክራሲው ወደ ጭቆናና አንገት መድፋት ተቀይሮ እየተረገጠና እየተገረፈ ሲያሠኛቸውም ወደ እስር በመወርወር አፉን አዘግተው እነሱ ግን የክብር ቦታቸውን እንደያዙ ቁጭ ብለዋል፡፡

ታዲያ መቸ ይሆን የዴሞክራሲያዊ ሁኔታዎች ሀገራችን ውስጥ ሲፈጠሩ፣ የሠብአዊ መብቶች ሲሸበሩ፣ የፍትህ መሰረት ሲጠናከር፣ የህግ የበላይነት ሲረጋገጥ የምናየው? ሕልማችን የሚፈታው ኢትዮጵያ ነጻ የምትወጣው መቸ ይሆን?

# ዴሞክራሲያውያን ነን ይላሉ ናቸውን?

**Thomas Demissie /Schwalbach**

ወያኔ ኢሕአዴግ እነሆ ስልጣን ላይ ከወጣ ሁለት አሰርት ዓመታት አስቆጥሯል። ወያኔዎች በጠመንጃ ስልጣን ከያዙ በኋላ እኛ ዴሞክራሲያዊ ነን እያሉ መለፈፍ ጀመሩ ተግባራቸው ግን በትክክል የዴሞክራሲያዊ ሃሣቡ የገባቸው አይመስለኝም። ምክንያቱም ላለፉት 20 ዓመታት የኢትዮጵያን ህዝብ በጎሣ በመከፋፈል በግፍ በአደባባይ በመግደል ከሃገር እንዲሰደድ በግፍ በማሰር በመደብደብ ኢትዮጵያ ለአንድ ብሄረሰብ ብቻ የሆነች እስኪ መስል እንደ ዳማ እየተጫወቱብን ይገኛሉ፡፡

ወያኔ በስልጣን ዘመኑ በባድመ ስም ብዙ ሺ ወገን እንዲረግፍ ያደረገ በጋንቤላ እና በኡጋዴን ተመሳሳይ ግፍ የፈጸመ አረመኔ መንግስት ነው፡፡ ይሕ አልበቃ ብሎት በ1997 ዓ,ም ወርሃ ግንቦት ለለውጥ የተነሣውን ሕዝብ በግፍ በማሰር በአደባባይ በመግደል ማንነቱን በግልጽ ያሣየ ነው፡፡ ደሃውን ገበሬ በማዳበሪያ ስም ሙልጭ አድርጐ የዘረፈ አሁን ደግሞ ነጋዴውን እንደአቅሙ ነግዶ እንዳያድር ከአቅም በላይ ግብር በማስከፈል ሰርቶ እንዳያድር በማድረግ ላይ ነው።

አሁን ደግሞ አሸባሪ እያለ እውነትን ለሕዝብ የሚያቀርቡ ንጹሕ ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞች በግፍ አስሮ እያሰቃየ ነው። ታዲያ ዲሞክራሲያዊያን ከሆኑ እንዴት የፕሬስ ሰዎች በግፍ ይታሰራሉ ምኑ ላይ ነው ዲሞክራሲ? እኔ እስከሚገባኝ ዲሞክራሲ ማለት ህዝብ በነጻነት ሀሳቡን መግለጽ ሲችል፣ ፕሬስ ከመንግስት ጭቆና ነጻ ሲሆን በህዝብ ምርጫ ወደስልጣን ሲመጣ የተሸነፈው በሰላም ለአሸነፈው ሲያስረክብ ስልጣኑን ይሕ ነው እውነተኛ ዲሞክራሲ እና እነዚህ ጐጠኛ ሰዎች ከሚሰሩት ግፍ እና አፈና አንጻር ዲሞክራሲያዊያን ናቸውን? መልሱን ለህዝቡ ልተወውና ወገኔ ለዚህ ኢ-ዴሞክራሲያዊያን ጎጠኛ ለሆነ መንግስት ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ለመብቱ ለክብሩ ብሎም ለሃገሩ ከመቼው ግዜ በላይ በቁጭትና በእልህ ተደራጅቶ በመታገል ህዝባዊ ሀይሉን በወያኔ ኢሕአዴግ አምባገነኖች ላይ ማሳረፍ አለበት፡፡ ድል እና ሰላም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሞት ለወያኔ!

# ግፍና ጭቆና ይብቃ

**Mekdes Fantahun /Tirschenreuth**

ከኢትዮጵያ ምድር ማንኛውም አይነት ጭቆና ከሕዝባችን ጫንቃ ተሽቀንጥሮ ተጥሎ የዜጐች እኩልነት

እንዲረጋገጥ አምርሮ መታገል አሁን እንደሆነ ገባኝ፡፡ በጨቅላ አእምሮአችን ባለማገናዘብ በየት/ቤት ባሉ የተባልነውን ስንል ዘምሩ የተባልነውን ስንዘምር ይሄን እርኩስ አረመኔ መንግስት ስንክብና ስናመሰግን ኖረናል፡፡ አሁን ግን በቃ ሁሉም ነገር በሰአቱ ይበቃል እንደሚባለው ማገናዘብ ስንጀምር ገባን፤ በወላጆቻችን ነገር በወንድም እህቶቻችን ባጠቃላይ በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለው ግፍና ጭቆና ተገለጸልን፡፡ ይህ ታዲያ ዛሬ እኛም ወያኔን ከሚቃወም አባል ጋር በመሆን ይሄን ግፈኛ መንግስት ለመበቀል ቆርጠን ተነስተናል፡፡

ወላጆቻችን በየስፍራው ተወርውረው አገር ተረካቢ ወንድሞቻችንና እሕቶቻችን አራት በአራት በሆነች ቆሻሻ ክፍል በብረት ተዘግተው ለነጻነትና ለአንድነት እንነሣ ባሉና ለመብታቸው በተከራከሩ ታፍነው ተወስደው ለቤተሰብ ሠቀቀን በመሆን ያሉበትን እንኳን ሣናውቅ ቀናት ቀናትን እየወለደ ይኸው አለን፡፡ እኛም ከቤተሰብ ተበትነን ቀረን፡፡

ይሕ እስከመቼ ይቀጥል ይሆን የኢትዮጵያ ሠፊ ሕዝብ ጥያቄ ግፍና ጭቆና መች ይሆን የሚያበቃው፤ ቀና ማለት የሚቻለንስ መች ይሆን፤ የሚታመነው መሪስ ማነው፤ እና እነዛን ያለፈ ስርአት ገዥ አምባገነኖች ተላቀቅን ስንል ነጻነታችን ታወጀ እያልን ስንምር ለካስ የባሰ መቶ ቁጭ ነው ያለልን፡፡ እውነት እ/ር ኢትዮጵያን ይጐበኛት ይሆን?አይቀርም!

# የወያኔ እውነተኛ ባሕሪ ሲገለጽ

**Ibrahim Seifu /Nürnberg**

ስልጣንን በሀይል የሙጥኝ ብለው የሃገራቸውን ሃብትና ንብረት ሲቦጠብጡ በኖሩት የሰሜን አፍሪካና የመካከለኛው ምስራቅ አገሮች አምባገነን መሪዎችን ላይ የደረሰው ሕዝባዊ ቁጣ ያስደነበረው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የመረጃ ፍሰት ለመገደብ በሁለት የስዊድን ጋዜጠኞች ላይ በደመ ነፍስ የወሰደው የድንጋጤ እርምጃ አገዛዙን በመላው አለም ይበልጥ እያጋለጠው እንደሚገኝ ታውቋል፡፡

በስዊዲን ሃገር በሚታተመው ታዋቂ ጋዜጦች፣ ሬድዮኖች፣ ቴሌቪዥኖች ላይ በተከታታይ እየወጡ ያሉት ዘገባዎች እንደሚያመለከቱት በወያኔ እስር ቤት ውስጥ ታጉረው ያሉት ሁለት የስዊዲን ጋዜጠኞች በኢትዮጵያ ውስጥ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ ነጻነትና መረጃን የማግኘት መብቶች ያለበትን አስከፊ ገጽታዎች አመልካች ናቸው ተብለዋል፡፡

የምእራባዊያን ጋዜጦችና ፖለቲከኞች ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ሥልጣን ላይ በተፈናጠጠበት የመጀመሪያዎቹ አመታት አፍሪካን ለመለወጥ ብሩህ አእምሮና ተስፋ ካላቸው ጥቂት መንግስታት ተርታ የሚመደብ ነው በማለት ሲያሞካሹት እንደነበረ እየገለጸ ያሉት የስዊዲን ጋዜጠኞች የመለስ ዜናዊ እውነተኛ ባህሪ የሆነው የአምባገነንነትና ጨቋኝነት ከምርጫ 97 ጀምሮ እራሱን እያጋለጸ መሆኑን በዜጐቹ ላይ እያደረሰ ያለው አፈና እስራትና ግድያዎች በማስረጃ በማጣቀስ ግልጽ የሆነ ትችት እያቀረቡበት ነው፡፡

እንግዲህ የወያኔ መንግስት ምን ያሕል አረመኔ እንደሆነ ተመልከቱ አለም አቀፍ ሽፋን ያላቸውን የስዊድን ጋዜጠኞች በዚህ መልኩ ካሰራቸው ምንም አይነት አለም አቀፍ ሽፋን የሌላቸውን ንጹሀን የኢትዮጵያ ዜጐችን እንዴት ሊያሰቃያቸው እንደሚችል መገመት አይከብድም፡፡

# አንድነታችን...

**Samuel Gebru /Tirschenreuth**

ጤና ይስጥልኝ ለመላው ጥላ መጽሄት አዘጋጆች በሙሉ ክብርና ምስጋና ለልኡል እግዚአሄር ይሁን እያልኩ በማስከተል ወደ እለቱ ጽሁፌ እገባለሁ፡፡

የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ለዘመናት አብረው ከመኖራቸው የተነሳ የሚያስተሳስራቸው የጋራ ባህሪ አላቸው ነገር ግን ይህን የጋራ ሀብት አዳብረው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሃይል እንዳይመሰርቱ ኢሕአዴግ የሚባለው /ዘረኛ አስተዳደር ወያኔ/ ድርጅት በጐሳ ላይ የተመሰረተ ሥርአት አምጥቶ መገነጣጠልን የሚያመቻች አንቀጽ 39 በሕገ- መንግስቱ በማስገባት ዘረኝነትና ክፍፍልን የሚያራመድ መርዘኛ ፖሊሲ በተግባር በመተርጐም ላይ ይገኛል፡፡

ታዲያ የዚህ ዘረኛ መንግስት አላማ ኢትዮጵያን እንደ ሀገር ዜጐቿን እንደ ሕዝብ ለማወደም የታለመ አይደለምን? የኢትዮጵያ ሕዝብ በዴሞክራሲ ሥርአት ሰብአዊ መብትና በሕግ የበላይነት እንዲሁም ለመልካም አስተዳደር የሚያደርገውን ትግል በተለይ ወጣቱ ወገኔ ሊረዳ ይገባል። ስለዚህም ይሕን ብሄራዊ አንድነታችንን መልሰን ለመገንባት ለትግል ተነስተናል፡፡

## ታላቅ የስብሰባ ጥሪ

የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ(ኢህአግዘ) የፊታችን ቅዳሜ ማርች 3/2012 ከቀኑ 14:00 ሰአት በኑረንበርግ ከተማ በኖርደንስባኖፍ መደበኛ የአባላት የስብሰባ ፕሮግራሙን ያካሂዳል።የግንባሩ አባላት የሆናችሁ በሙሉ በስብሰባው እንድትገኙለትም ጥሪውን ያቀርባል።ለበለጠ መረጃ የግንባሩን መረጃ- መረብ www.eppfguard.net ይጎብኙ!!!






## ጠላፊው"...

የዚህን ሰው ስልክ መጥለፉ ይብቃ ልላቸው ነበር። ነገር ግን እርሳቸው የጠረጠሩትን እንደማይጠረጠር አድርጎ መቁጠር ትልቅ ድፍረት ሆኖ ተሰማኝ። ታድያ እስከ መቼ ራሴን እየፈተንኩ እዘልቀዋለሁ። አስቤ አስቤ ክስ አገኘሁ።

አሁን ወሰኛለሁ። ይሄ ጎረምሳ መከሰስ አለበት እኔም የእሱን ስልክ በመጥለፍ ወንድኔቴን የማስጨንቅበት ምክንያት የለም። አዎ ጠለፋዬ አብቅቷል ብዬ ሪፖርት ማደረግ። ከዛም ክስ እንዲመሰረት መጠየቅ አለብኝ። አለቃዬ ዘንድ ቀርቤ የጠለፋ ስራዬን በአግባቡ እንደጨረስኩና አጠቃላይ ሪፖርት ማቅረብ እንደምችል ተናገርኩ።

በሪፖርቴም ይህ ወጣት የተሰማራበት የሽብር ስራ ከዚህ በፊት ያልተለመደ እና እጅግ ውስብስብ አካሄድም እንዳለው ገለፅኩ።ወጣቱ በፍቅር ስም የሚያሰባስባቸውን ኮረዶች የዜጎችን የመደራጀት እና የመስራት አቅም የሚያዳክም ከመሆኑም በላይ ሴቶቹ በማህበር ተደራጅተው አምራች ዜጋ እንዳይወጣቸው አስተጓጉሏቸዋል። ይህንንም እጅግ በተቀነባበረ መልኩ እንደሚሰራ አስረዳሁ። አንድ ክፍለጦር የሚሆኑ ሴቶችን የሚጋብዝበትም የገንዘብ ምንጭ ሊጣራ የሚገባው ነው። ከዛም በተጨማሪ በተደጋጋሚ በሚደውላቸው ስልኮች ረጅም ሰዓት ስለሚይዛቸው የአካባቢውን ኔትዎርክ ስራ እንዲበዛበት አድርጓል። ይህም የቴሌ ተቋምን ከማፈራረስ ተለይቶ አይታይም። ስልም ጨመርኩለት።

በአሁኑ ግዜ ወጣቱ በውስብስብ የሽብር ስራ ተጠርጥሮ ምርመራ ላይ ይገኛል። እኔም ወጣቱ ዘወትር ምሽት በስልክ በሚሰራው ፍቅር ወንድነቴን ከመፈተን ድኛለሁ።አንድ ምስጢር ግን ልንገራችሁ... በወጣቱ ስልክ ጠለፋ ባዳበርኩት ልምድ መሰረት በርካታ ቆነጃጅትን ለማባበል እየተጋሁ ነው። እስከ አሁን በቅጡ አልተሳካልኝም። ነገር ግን ቀድቼ ያስቀመጥኩትን የዛን "አሸባሪ" ወጣት ጥበብ ደጋግሜ እየሰማሁ ደጋግሜ እሞክራለሁ። (አትሳቁብኝ ጥቅማ ጥቅማችን እኮ ይቺው ናት!) ወዳጄ የዛሬው ሀሳብ ወለድ ጨዋታችን በዚህ ያበቃል... አማን ያሰንብተን!

# CATCH-22

**Dawit Fanta (Engineer)**
**Germany.**

"Catch-22" is a term coined by an American novelist Joseph Heller in his novel Catch-22, describing a set of rules, regulations or procedures, or situation which presents the illusion of choice while preventing any real choice. For example, you can't get a job without experience, but you can't get experience unless you have a job; it is catch-22.

While I was surfing internet last December 2011, I saw the dictator Meles Zenawi warmly shaking hands with the governor of Exim (Export Import) Bank of China at his office. Of course the arrival of the governor (one of the economic hitman of china) was for further deal on tremendous sum of debts to Ethiopia. Actually if you dig down into the deal, it would say metaphorically like this: "we are going to loan you billions of dollars on the condition that the money will be earmarked for the construction of infrastructure and all projects will be contracted out to our country's companies. And those companies will be free even to bring human resource from our country and keep in mind that you will pay us back our money with attractive interest in a scheduled period of time."

As a matter of fact, herein lies the little nightmare of Zenawi's "Two Digit Economic Growth" paradox; meaning that "in order for Ethiopia grow up economically, we have to have loan; and to pay back our loan, we have to grown up economically"; which is a clean case-in-point Catch-22 dilemma.

But why a country like Ethiopia which has all possible resources to grow up becomes mainly lean on debt? How a country with numerous registered heritages by UNESCO fails to attract tourists unlike Egypt does? How a country with leading rank in cattle breeding in Africa fails to export or process meat and hides unlike Botswana does? Why a country with highland coffee, Tea and favourable weather for horticulture fails to succeed unlike Kenya does? How a country with more than five major cross country rivers fails to construct irrigation system and feed its own people?

Apparently, the root cause for all these failures is overlooked political issues, i.e. the more we fail to solve our political problems, the more we make wrong policies which lead us into abject poverty and then soaked us into unbearable national debt.

Yet in spite of focusing on how to resolve political problems, the current regime is trying to evade from the truth and is going to suppress our political demand by inflicting the following abusive acts:

- Citizens are subjected to torture, to cruel, inhuman and degrading treatment and punishment.
- Ruling party members are favoured socially and financially.
- Citizens are subject to arbitrary arrest and detention.
- Citizens particularly those who are charged with a political case have been humiliated and sometimes not presumed innocent before proved guilty, or stay long in prison without justice.
- Citizens haven't the right to freedom of opinion and expression. Free presses are crippled and set up to fail by ratifying different decrees. Journalists are persecuted; some of them are either in exile or jail. Leave alone Ethiopian journalists, the despotic regime of Zenawi has sentenced two

Swedish journalists on December 27, 2011, to 11 YEARS in prison under the fake charge of "Supporting terrorism and entering the country illegally." Actually, freelance reporters Johan Persson and Martin Schibbye were on the journalistic mission when they were captured on July1, 2011. Consequently, the country is in the black list of CPJ.

- Citizens haven't the right to freedom of peaceful assembly and association, and they are forced to belong to the ruling party in one or another way.

So, no matter how the fact is like this, the dictator Zenawi and his circle are still enjoying their denial of fact. And they know and we also know the reason why they put the country into such swamp of debt; it is just to maintain their power by bluffing as if there is a development and to get personally a huge sum of commission from the foreign Creditor Banks at the country's cost.

For the last twenty solid years we have been host for Zenawi's parasitic regime but now we have to break the silence of this catch-22 situation and fight by all possible means until we derive the last nail into his coffin as the Libyan free fighters did on the dictator Gaddafi.

# Oromiya is calling!

**Askal Abera/Bad Camberg**

I would like to explain what the EPRDF regime doing on the people of Oromo. By all accounts, that the TPLF regime murdered many Oromos` every year. It looks TPLF is determined to turn every inch of Oromo territory in to killing fields. Youth, women, children, and the elderly are murdered everywhere. People are shooting in school, on the streets, in their houses and in the detention centers.

There are always tortures. Peoples are beaten up day and night. Our places are very worrisome. So, the people of Oromo should have to stand and struggle together to be free from the colonial administration of TPLF/EPRDF.

Especially people who are living in different parts of the world have the responsibility to reveal the mal-administration and anti-democratic activities of Woyane against the Oromo people to donor agencies. Long live to Oromiya!!!

# A war Lover Regime!

**Bisrat Weldemikael/Bisrat Girer- Stadt Aßlar**

Today our motherland Ethiopia is found under the brutal regime of beggars who are stealing everything worthy and transfer it to their account. Our mother country is ruined and became the house of the world's poorest people. It is really becoming increasingly shameful to be an Ethiopian.

Recently, Woyane has killed and kidnapped foreigners in northern Ethiopia, the Danakil areas. As usual, it is blaming the Eritreans for that when the real fact is that Ethiopian freedom fighters, which Woyane ignore to exist, are trying to have their voice heard.

Woyane's prime beggar, Meles, using this as a pretext, said that his minority regime will start war against Eritrea to change the focus of Ethiopian people.

It is as if my day-dream gets fulfilled if Woyane would do that, for then it will be his last day. Today, Amharas and Oromos, the biggest ethnic groups of Ethiopia, are ready to desert the army, if war

broke out. This war will be their war, that of woyanes.

It will not be like that of 1998-2000, but very short and the last one in this region. Believe me; Woyane will go once and for all. Most of Ethiopians whom I met are saying: let us give those beggars the last chance so that we can concentrate on our economic developments together with the genuine peace loving citizens.
So, we must prepare ourselves for all eventualities. 2012 will be our year, the year of development, peace and harmony with avoiding a pro-war Woyane regime!
A united and peaceful Ethiopia will prevail

# Harassment tool- `` Ethiopian Anti-terrorism law``

**Genet Zewdie/Duisburg**

The political behavior of Ethiopia's ethnic minority regime and the economic and social stability of Ethiopia have been continuously deteriorating after the infamous May 2005 election.

After yet another staged election in 2010, and especially after waves of demonstrations and protests rooted out dictators in North Africa, PM Meles Zenawi's ethnic regime reduced itself into a small group of outlaws that use the legal system as a core to round up dissenters and ship them to prison camps.

In its futile attempt to prevent the inevitable, PM Zenawi's dictatorial regime has literally stopped functioning as a state and has devoted the bulk of its time to eavesdropping harassing, arresting, and killing otherwise law abiding citizens in the name of 'terrorism'.

In the last two months, the brutal regime in Addis Ababa has detained and falsely charged foreign and domestic journalists, civil right activists, political party leaders and nationally notable individuals. For example, Woubshet Taye of the Awramba Times, Reeyot Alemu of Feteh newspaper, Bekele Gerba of the Oromo Federal Democratic Movement, Oblana Lelisa of the Oromo People's Congress and the two Swedish journalists from the kontinent News Agency are some but few of the recent victims of Ethiopia's restrictive and equivocal counter-terrorism law. All of the above individuals including the two Swedish journalists were detained and condemned with fabricated charges and under the pretext of working with or for 'terrorist' organizations.

Based on the above hard facts, if any one who engages in any opposition political parties or if anyone who writes an article against an Ethiopian Dictatorial regime, he/ she is automatically black listed as a terrorist or a pro terrorist groups by the regime.

So, it is a very critical time to Ethiopians who reside all over the world to reveal or use their right of freedom of expression. The solution is one and obvious. That is, we should have to unite together and fight against the dictatorial regime of Ethiopia.

# Stop killing of the Oromo people!

**Hawi Beka/Alsfeld**

It is known that the suffering of the Oromo people increased from day to day. The international community has remained in different to the harassment of the Oromo people. In some cases, the International Communities are helping the dictatorial government to sustain its corrupt system which would have fallen apart under its own

weight.

Many Oromo people are beaten and killed in the day light on the streets of all Oromia zones. Thousands are arrested in different jails without any reason and question. students are tortured and killed every day by Woyane`s security forces. Farmers are taken from their lands and harassed.etc.

And also, many of them are migrating to different countries of the world. All these Woyane regime activities are a State sponsored terror activities. Unless urgent actions and measures are undertaken by all Oromo people in an effort, Meles Zenawi never stops his murderer activities.

For how long, the killing and arresting will continue? Wake up the Oromo people! Get up stand up, Stand up for your right!!!Long Live to OLF!!!

# Nothing Pass People´s voice

**Samuel Eshetu /Nürnberg/**

The last 20 years have clearly nacked the poor behavior of the tyrannic government of Ethiopia that it is not ready for any peaceful dialog and its inability to listen the voice of the people for freedom and democracy.

The regime does not respect the principles of democracy, human rights and rule of law. Instead, it is engaged in terrorizing and suppressing the people for the sake of prolonging its power.

